Centre for Information Resilience

# መደበኛና የማይሰተዋል:

# በኢትዮጵያ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ስለሚታዩ ፆታዊ የጥላቻ ንግግሮች ትንተና

The Centre for Information Resilience

February 2024


# 1. አጠቃላይ ሃሳብ

የሰዎች ግላዊና ማህበራዊ ህይወት ኢንተርኔት ላይ በሰፊው መንፀባረቅ መጀመሩ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ አዲስ ፈተና ሆኖ ብቅ ብሏል። ኢንተርኔት መረጃን ለማሰራጨት፣ ማህበራዊ ትስስርን ለማጎልበትና የፖለቲካ አንቅስቃሴና አክቲቪዝምን ለማሳላጥ ከመጥቀሙ ጎን ለጎን በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ላደረገ ጥቃትና መድሎ መፈፀሚያ መድረክ እየሆነ ይገኛል።

ዘ ሴንተር ፎር ኢንፎርሜሽን ሪዚሊየንስ (ሲ.አይ.አር) ኢትዮጵያ ውስጥ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ባደረገ ጥቃት ዙሪያ የሰራው ጥናት፣ አዲስ አበባ ውስጥ በጉዳዩ ላይ የተደረጉት ውይይቶች እና ይህ በጥላቻ ንግግር ዙሪያ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳዩት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሴቶችና ልጃገረዶች የጥላቻ ንግግርና ትንኮሳን ጨምሮ የተለያዩ አይነት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ተጠቂ ናቸው።

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ከመጀመሪያውም በነበሩ ታሪካዊ ፣ ሀይማኖታዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ አመለካከቶች ላይ የተመረኮዙ ናቸው (ምስል 1)። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን መከላከል ኢንተርኔት ላይ የሴቶችና የልጃገረዶችን ደህንነት ከማስጠበቅ አልፎ በሁሉም ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያግዛል ። የዚህ ፕሮጀክት ዓላማዎች እንደሚከተሉት ናቸው፡


- ኢትዮጵያ ውስጥ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ያለውን ማስረጃ ማጠናከር
- የመንግስት ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎችና ማህበረሰቡ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ስላደረጉ ጥቃቶች ያላቸውን ግንዛቤ ማጠናከር
- በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን በመከላከል ዙሪያ ለሚሰሩ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የመንግስት ተቋማት ተግባራዊ ምክረ ሀሳቦችን ማቅረብ




*ምስል 1፡ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች የሚያበረክተውን የመገለል ዑደት ለማሳየት ሥዕላዊ መግለጫ።*

## ቁልፍ ግኝቶች

ይህ ፅሁፍ ኢትዮጵያ ወስጥ በሶስት ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ (ፌስቡክ፣ ቴሌግራምና፣ ኤክስ) የሚፈፅሙትን ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ቁጥራዊ በሆነ ሁኔታ በማጥናት ሲ.አይ.አር “በኢትዮጵያ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሴቶችን ኢላማ የሚያደርጉ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች” በሚል ርዕስ የሰራውን ጥናት የሚያጠናክር ነው ነው ።[1]




*ምስል2: የጥናቱን ዲዛይንና የትርጓሜ ሂደት የሚያሳይ የሲ.አይ.አር ሃሳባዊ ማዕቀፍ*

[1] የዚህ ጥናት የጥናት ዘዴና ሃሳባዊ ማዕቀፍ “Resources for African Indigenous Languages” በተባለው ትምህርታዊ ህትመት ላይ ይካተታል። ይህን ማስፈንጠሪያ ተጠቅመው ይመልከቱ፡ https://sadilar.org/en/the-fifth-workshop-on-resources-for-african-indigenous-languages-rail/

ሲ.አይ.አር አዲስ አበባ ውስጥ ውይይቶችና አውደ ጥናቶችን በማካሄድ በአራት ቋንቋዎች (አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛ እና እንግሊዘኛ) የጥላቻ ንግግሮችን ከኢንተርኔት ላይ ለመለየት የሚያግዙ 2058 ጥቃት አዘል ቃላቶችን መርጧል። እነዚህን ቃላት የያዙ 327,343,548 የማህበራዊ ሚዲያ ልጥፎች ከተለዩ በኋላ 7005ቱ ልጥፎች በጥቃቶቹ አውድ፣ አይነትና ኢላማ መሰረት ተለይተዋል (ከላይ በሃሳባዊ ማዕቀፉ ላይ እንደሚታየው)።

ይህም ጥናት ሆነ ሲ.አይ.አር ከዚህ በፊት ያካሄደው ጥናት ሴቶችና ልጃገረዶች ከወንዶች በአይነት የተለየ የኢንተርኔት ላይ ጥቃት እንደሚደርስባቸው አሳይተዋል። የመጀመሪያው ጥናት ላይ የተሰተፉት የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች እንደገለፁት ሴቶችና ልጃገረዶች የተሳሳቱ የስርዓተ-ፆታ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁና ሴትን ዝቅ የሚያደረጉ ጥቃቶች ሲደርሱባቸው ወንዶች ግን በአብዛኛው ባንፀባረቁት ሀሳብና ፖለቲካዊ አመለካከታቸው ዙሪያ ጥቃት ይደርሰባቸዋል። በዚህ ጥናት ላይ የተሰራው የማህበራዊ ሚዲያ ትንታኔ ሴቶችና ልጃገረዶች ከወንዶች በበለጠ ሁኔታ ፆታን መሰረት ያደረጉና ፌዝ ወይም ስላቅ የያዙ የጥላቻ ንግግር እንደሚደርስባቸው አሳይቷል።[2] በተጨማሪም ብሔር እና ሀይማኖትን የመሳሰሉት ማንነቶች ተጨማሪ ኢላማ ሲሆኑ በሴቶች ላይ ያለው የኢንተርኔት ጥቃት ስጋት እንደሚጨምር ጥናቱ ቃኝቷል።

በተደረጉ ውይይቶችና አውደ ጥናቶች መሰረት በጥላቻ ንግግር ዙርያ ያለው የተሳሳተ አመለካከት አንዳንድ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ትኩረት እንዳይሰጣቸው አድረጓል። ለምሳሌ የተሳሳቱ የስርዓተ-ፆታ አስተሳሰቦችን የሚያንፀባርቁ ንግግሮች፣ ስድቦች፥ አዋራጅ ንግግሮች ወይም ሴቶችና ልጃገረዶች ከወንዶች ያነሱ እንደሆኑ የሚያትቱ ሃሳቦች፤ ዘቻና ጠብ ጫሪ ከሆኑ የጥላቻ ንግግሮች አንፃር ያነሰ ጉዳት እንደሚያመጡ ይታሰባል። በአንዳንድ ወይይቶች ላይ እንደ ጥላቻ ንግግር ያልታዩበት ሁኔታም ነበር። ስለዚህም ኢትዮጵያ ወስጥ ስለ ጥላቻ ንግግር ምንነትና ተፅዕኖዎቹ ማስተማር አስፈላጊ ነው ።

ሲ.አይ.አር ከዚህ በፊት በሰራው ጥናት ላይ ተሳታፊ የነበሩ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች በተጠቀሟቸው ሁሉም የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንደተመለከቱ ገልፀዋል ። በጥናቱ መሰረት በሶስቱም ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ያሉ ሴቶችና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች በአውድ ቢመሳሰሉም በአይነት ግን ይለያያሉ። ለምሳሌ ስድቦች ኤክስ የሚባለው ማህበራዊ ትስስር ገፅ ላይ በብዛት ሲታዩ ቴሌግራም ላይ ደሞ ዘቻዎች ይበዛሉ። ፌስቡክ ላይ አንድን ጾታ በጅምላ ከአንድ ባህሪ (ለምሳሌ ከስግብግብነት) ጋር የሚያገናኙ ወይም ሴቶችና ልጃገረዶች ባላቸው ማህበራዊ ተሰሚነት፣ አስተሳሰብና አካላዊ ብቃት ዝቅ አድርገው የሚያሳዩ የጥላቻ ንግግሮች ይበዛሉ። በማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች መካከል ያሉትን ልዩነቶች መረዳት፣ ችግሩ ላይ ያነጣጠረ መፍትሄ ለመስጠትና ሴቶችና ልጃገረዶች በኢንተርኔት ላይ ደህንነታቸውን እንዲጠብቁ የተሻለ መረጃ አንዲኖራቸው ይረዳል። አንድ የመፍትሔ ሀሳብ ለሁሉም የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ወይም ተጠቃሚዎቻቸው ላይሰራ ይችላል ።

በተጨማሪም ሴቶችና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ሌሎች ማንነትን መሰረት ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች አንደሚለዩ ይህ ጥናት ተመልክቷል። ሴቶችና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ብሔርንና ሀይማኖትን መሰረት ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች በበለጠ መልኩ የበታችነትን የሚሰብኩ፣ በማህበራዊ ሚና ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁና ፌዝ ወይም ስላቅን ያዘሉ ናቸው። በተጨማሪም ከኢንተርኔት ውጪ ያሉ ወቅታዊ ሁነቶች ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ያሉ ክርክሮችና የጥላቻ ንግግሮች ላይ ተፅዕኖ እንዳላቸው ጥናቱ

[2] የጥቃቶቹ አይነት በሃሳባዊ ማዕቀፉ ላይ ተብራርተዋል

ተረድቷል። ለዚህ ጥናት መረጃ በተሰበሰበበት ወቅት በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች በነበረው ግጭት ምክንያት የአማራና የኦሮሞ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ያነጣጠሩ የጥላቻ ንግግሮች መጨመራቸው የዚህ ማሳያ ነው። ፖለቲካዊ ሁነቶችን ተከትለው የሚመጡና ጠብ ጫሪ የሆኑ የጥላቻ ንግግሮች ፆታን መሰረት ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች አንፃር ትኩረትን ይስባሉ። ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች እጅጉን ከመለመዳቸው የተነሳ ትኩረት እንደማይሰጣቸው የአውደጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል ።

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሴቶችና ልጃገረዶች መገለል ምክንያት የሆኑ የጥላቻ ንግግር አይነቶችን ለመዳሰስ ያለመ ነው። ሲ.አይ.አር ከዚህ በፊት ባጠናው ጥናት ላይ በቃለ መጠይቁ የተሳታፉት ሴቶች በደረሰባቸው የኢንተርኔት ጥቃት ምክንያት ዝምታን እንደመረጡና ራሳቸውን ከኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ውጪ ካሉ መድረኮች እንዳገለሉ ገልፀዋል። ለሴቶችና ልጃገረዶች ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርኔት መድረክ መፍጠር በማህበራዊ ህይወት ውስጥ የተሟላና ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ያበረታታል። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚቀረፁ ስትራቴጂዎች የችግሩን ስርወ-ምክንያት ያማከሉ መሆን አለባቸው። ይህም ሴቶችን የሚያገሉና በፆታዊ ሚና ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አስተሳሰቦችን ማሻሻልና ሴቶችና ልጃገረዶች በተለያዩ ማህበራዊ ዘርፍ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ማጠናከርን ያካትታል።

## ምክረ-ሃሳቦች

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች መልክ (የጥቃቶቹ ዓላማ፣ የሚፈፀሙበት መድረክ ፣ እንዴት እንደሚፈፀሙ) ዙሪያ ጥናት ማድረግ እያንዳነዱ ችግር ላይ ያነጣጠረ መፍትሄ ለመስጠት ያስችላል። በተያያዘ ሲ.አይ.አር ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመስራት ፖሊሲዎችንና ማህበረሰብ መር የሆኑ የመፍትሔ ሀሳቦችን የያዘ ሰነድ ከዚህ ሪፖርት ጋር አዘጋጅቷል ።

ይህ ጥናት የጥላቻ ንግግሮች እንደ ኢላማቸው እንደሚለያዩ አሳይቷል። እነኚህን ልዩነቶች መረዳት ለችግሮች ተስማሚ የሆነ መፍትሄዎችን በመስጠት ሴቶችና ልጃገረዶች ኢንተርኔት ላይ ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ማድረግ ይቻላል። ሲ.አይ.አር የዚህ ጥናት ውጤት የመንግስት ተቋማት ውሳኔዎችን ለማሳለፍ፣ ማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች የይዘት ቁጥራቸውን ለማሻሻል ፣ ሲቪል ማህበራት ድምፃቸውን ለማሰማትና ማህበረሰቡ ደግሞ ለለውጥ ጥሪ እንዲያቀርቡ ያግዛል ብሎ ያምናል ።

# ማውጫ

**1. አጠቃላይ ሃሳብ ........ 2**

ቁልፍ ግኝቶች ........ 3

ምክረ-ሃሳቦች ........ 5

**ማውጫ ........ 6**

**2. መግቢያ ........ 8**

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ስላደረገ ጥቃት ማጥናት ለምን አስፈለገ? ........ 9

የፕሮጀክቱ ግቦች ........ 10

የጥናቱ ጥያቄዎች ........ 10

የጥናቱ ወሰን ........ 11

**3. የጥናቱ ዘዴ ........ 12**

ሃሳባዊ ማዕቀፍ ........ 12

ቃላትን ማሰባሰብ ........ 14

የመረጃ አሰባሰብ ........ 15

*3.3.1. ኤክስ (በቀድሞ ስሙ ትዊተር) ........ 16*

*3.3.2. ቴሌግራም ........ 16*

*3.3.3. ፌስቡክ ........ 16*

የመረጃ አዘገጃጀት ........ 17

*3.4.1. የመረጃ ቅድመ ዝግጅት ........ 17*

*3.4.2. መረጃዎችን የጥላቻ ወይም የጥላቻ ያልሆኑ/ሰላማዊ ብሎ መመደብ ........ 18*

*3.4.3. ለቀጣይ ትንተናዎች የመረጃ ናሙና መረጣ ........ 19*

*3.4.4. በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች የመረጃ አዘገጃጀት ሂደት በቁጥር ........ 19*

የመረጃ ትርጓሜ ........ 20

*3.5.1. የመረጃ ተረጓሚዎች ........ 20*

*3.5.2. በተርጓሚዎች መካከል ያለ ስምምነት ........ 21*

ውይይቶችና አውደ ጥናቶች ........ 21

ውስንነቶች ........ 22

*3.7.1. ቋንቋዎች ........ 22*

*3.7.2. መረጃ አሰባሰብ ........ 22*

*3.7.3 የመረጃ ዝግጅትና አመራረጥ ........ 25*

*3.7.4. ተደረሪቢ ጥቃቶች ........ 25*

*3.7.5. የመረጃ ትርጓሜ ........ 25*

**4. ውጤቶችና ውይይቶች ........ 27**

4.1 ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ ፆታዊ የጥላቻ ንግግሮች ........ 27

4.1.1. ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አይነቶች....27

4.1.2. ሴቶችን ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አውዶች....29

4.1.3. ማብራሪያ፡ ሴቶችንና ልጃገዶችን ኢላማ ያደረጉ  የጥላቻ ንግግሮች....30

4.2 ሴቶችንና ልጃገረዶችን ብቻ ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች በመድረክ....31

4.2.1. ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አይነቶች በመድረክ....32

4.2.2. ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አውዶች በመድረክ....32

4.2.3. ማብራሪያ፡ ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች በመድረክ....33

4.3 ፆታዊ ንፅፅር....34

4.3.1. የጥላቻ ንግግር ከፆታ አንፃር....34

4.3.2. የጥላቻ ንግግር አይነቶች በፆታ....35

4.3.3. የጥላቻ ንግግር አዉዶች በፆታ....36

4.3.4. የጥላቻ ንግግርና የፆታ ንዑስ ቡድኖች ግንኙነት በመድረክ....37

4.3.6. ማብራሪያ፡ የጥላቻ ንግግር በፆታ ንዑስ ቡድኖች....38

4.4 ከሌሎች የጥላቻ ኢላማዎች ጋር ንፅፅር....38

4.4.1. ህጋዊ ከለላ ያገኙ ማንነቶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች....39

4.4.2. የጥላቻ ንግግር ከጥላቻ ኢላማ ንዑስ ቡድኖች አንፃር....39

4.4.3. የጥላቻ ንግግር አይነቶች ንፅፅር....40

4.4.4. የጥላቻ ንግግር አውዶች ንፅፅር....41

4.4.5. ማብራሪያ፡ ከሌሎች የጥላቻ ኢላማዎች ጋር ንፅፅር....42

4.5 ተደራራቢ ፆታን መሰረት ያደረገ የጥላቻ ንግግር....43

4.5.1. ተደራራቢ የጥላቻ ንግግሮች....43

4.5.2. የተደራራቢ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃት አይነቶች....44

4.5.3. የተደራራቢ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃት አውዶች....45

4.5.4. ማብራሪያ....46

4.6 የግብረ ሰዶማዊነት ውንጀላዎች....47

**5. መደምደሚያ....49**

**6. ምክረ ሀሳቦች....51**

## 2. መግቢያ

ኢንተርኔት በኢትዮጵያ ውስጥ ተቃራኒ ተፅዕኖዎች ያሉት መድረክ ነው። መረጃን ለማሰራጨት፣ ማህበራዊ ህይወትን ለማጎልበትና አክቲቪዚምንና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን ለማሳለጥ ቢጠቅምም በስተጓዳኝ በቴክኖሎጂ ድጋፍ ለሚቃጡ ፆታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች መፈፀሚያ መድረክም እየሆነ ነው ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አዋቂም ሆኑ ወጣት ወንዶችና ሴቶች የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ሰለባ እንደሆኑ ጥርጥር የለውም።[3] ሲ አይ አር እ.ኤ.አ በ 2023 "በኢትዮጵያ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሴቶችን ኢላማ ያደረጉ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች"[4] በሚል ርዕስ ባጠናው ጥናት ላይ የተዛማጅ ፅሁፎችን ምልከታ በማድረግና በኢትዮጵያ ውስጥ በሚዲያና ሲቪል ማህበረሰብ ውስጥ ጨምሮ ትልልቅ ቦታ ያላቸው 14 ሴቶችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ ተጎጂዎች በኢንተርኔት ጥቃት ዙሪያ ስላላቸው ልምድና ስለ ተፅዕኖዎቹ ለመረዳት ሞክሯል። የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎችም ጥቃቶቹ ኢላማ እንዳደረጉት ፆታ በአውድ፣ አላማ ወይም በሚፈጥሩት ተፅዕኖ እንደሚለያዩ ገልፀዋል። ኢንተርኔት ላይ ያለው ጤናማ ያልሆነ ሁኔታና ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ያነጣጠረ የኢንተርኔት ላይ ጥቃት፤ ሴቶችና ልጃገረዶች ማህበረሰቡ ውስጥ ስላላቸው ሚና ያለውን የተዛባ ማህበረሰባዊ አመለካከት የሚያሳይ እንደሆነ የጥናቱ ግኝቶች ያመለክታሉ።

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሰፊ የሆኑ ጎጂ ባህሪያትን ቢያካትትም ሲ.አይ.አር በዚህ ጥናት ላይ በጥላቻ ንግግር ላይ በማተኮር ከኤክስ (በቀድሞ ስሙ ትዊተር)፣ ቴሌግራም እና ፌስቡክ ላይ የተገኙ ልጥፎችን በቁጥራዊ መንገድ ተንትኗል። የመረጃ አሰባሰቡን ለማገዝ እንዲረዳ በማሰብ በአራት ቋንቋዎች (አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛና እንግሊዘኛ) ጥላቻ አዘል የሆኑ ቁልፍ ቃላት እንዲሰበሰቡ ተደርጓል ። ልጥፎች ከተመረጡ በኋላ በሶስት መስፈርት እንዲለዩ ተደርጓል፤ በጥቃቶቹ አላማ፣ አይነትና አውድ።[5] በተጨማሪም ይህ ጥናት በፆታ ላይ ከሚሰነዘሩ የጥላቻ ንግግሮች በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንግስት የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ባወጣው አዋጅ ላይ ህጋዊ ከለላ ያገኙ ማንነቶች (አካል ጉዳተኝነት፣ ብሔር፣ ዘር፣ ፆታ፣ ሀይማኖት[6]) ላይ የሚፈፀሙ የጥላቻ ንግግሮችንም ጭምር ያጠናል። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ከሌሎች ማንነቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጥናት በመጀመሪያው ጥናት ላይ አስፈላጊነቱ ታይቷል ።

አዲስ አበባ ውስጥ በተደረጉት ውይይቶች ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሴቶችና ልጃገረዶች የጥላቻ ንግግርን ጨምሮ ሰፊ የሆኑ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንደሚደርስባቸው በሁሉም ዘንድ የተነሳ ሀሳብ ነበር። በጉዳዩ ላይ ያለው የመረጃ እጥረት ችግሩን ለመፍታት እንቅፋት እንደሆነ የውይይቱ ተሳታፊዎች ገልፀው ነበር። ይህ ጥናት ኢትዮጲያ ውስጥ ሴቶችና ልጃገረዶች በሶስቱ ታዋቂ የማህበራዊ ሚዲያ ትስስር ድህረ-ገፆች

---

[3] ሲ አይ አር እ.ኤ.አ በ2023 "በኢትዮጲያ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሴቶችን ኢላማ ያደረጉ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች" በሚል ርዕስ የሰራው ጥናት በሲ.አይ.አር ድህረ-ገፅ ላይ ይገኛል

[4] Ibid.

[5] የጥላቻ ንግግር አይነትና አውድ ትርጓሜ ክፍል 7.1 ላይ በሚገኘው ትርጓሜ ፕሮቶኮል ላይ ይገኛል።

[6] የአዋጅ ቁጥር 1185/2020፣ የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ላይ እንደሚታው (እ.ኤ.አ 2020)፣ ይህን ማስፈንጠሪያ ይጠቀሙ https://ethionab.org/wp-content/uploads/2022/09/1185_2020_HATE_SPEECH_AND_DISINFORMATION_PREVENTION_AND_SUPPRESSION_PROCLAMATION_.pdf

(ኤክስ፣ ቴሌግራምና ፌስቡክ) በሚደርስባቸው የጥላቻ ንግግር አይነትና አውድ ዙሪያ ያለው የመረጃ ክፍተት ለመሙላት ያለመ ነው ።

## በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ስላደረገ ጥቃት ማጥናት ለምን አስፈለገ?


በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ራሱን የቻለና ጐጂ የሆነ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት አይነት ሲሆን ሴቶችና ልጃገረዶች በዲጂታሉና በእውነተኛው ዓለም ላይ የሚደርስባቸውን መድሎ የሚያባብስም ነው። ይህም በተጎጂዎች ላይ ዘላቂ የሆነ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳቶችን ያስከትላል።

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የፍርሀትና የመሸማቀቅ ስሜትን በመፍጠርና ሴቶች ኢንተርኔት ላይ ደህንነት እንዳይሰማቸው በማድረግ ኢንተርኔት ላይና ከኢንተርኔት ውጪ ያላቸውን የማህበራዊ ተሳትፎ ይገድባል። ይህ መገለል ፍትሃዊ ውክልና የሌለው ማህበረሰብንና የዴሞክራሲ ሂደትን ያስከትላል።

በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የመገለልና የመድሎ ዑደቶችን የሚያስቀጥሉ ናቸው። ይህ አይነት ጥቃት በፆታ አግላይ የሆኑና የወንዶችና የበላይነት የሚያንፀባርቁ አስተሳሰቦች ውጤት ሲሆን በታሪክዊ፣ በሀይማኖታዊ፣ በፖለቲካዊ እና በባህላዊ አመለካከቶችም ውስጥ የተቀበረ ነው። እነዚህ እምነቶችና አስተሳሰቦች ጥቃቅን፣ ቀጥተኛ ላልሆኑና ባለማወቅ ለሚደርሱ መገለሎችና ጭፍን ጥላቻዎች መሰረት ይሆናሉ። እነኚህ ግልፅ ያልሆኑና የማይታዩ የመገለል ድርጊቶች ወደቃላት ጥቃቶች ማለትም ወደ ስድቦች፣ ዛቻዎችና ማስፈራሪያዎችን ያድጋሉ። በተጨማሪም እስራት፣ ወከባና አካላዊና ወሲባዊ ጥቃቶች ለመሳሰሉ አካላዊ ጉዳቶች በር ይከፍታሉ። ጥቃቶቹም እዚህ ደረጃ ከደረሱ በኃላ ተጠቂዎች ላይ ዘላቂ የሆነ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት የማድረስ እድላቸው ከፍተኛ ነው። በመጨረሻም ሴቶችና ልጃገረዶች ሀሳባቸውን እንዳይገልፁ በመገደብና በማግለል በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ሰጪነት ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል። ሴቶችን ጨምሮ የሌሎች ቡድኖች ሃሳቦች ብዝሃነት አለመኖር የመንግስት አካላት ስልጣን ተቀባይነት ላይ ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል።

ፆታን መሰረት ያደረጉ የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች ሴቶችና ልጃገረዶችም ላይ ሆነ ማህበረሰቡ ላይ ዘላቂ የሆነ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ። ሲ.አይ.አር ከዚህ በፊት ባካሄደው ጥናት ላይ በኢትዮጵያ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ከሚያደርጉና ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ከደረሰባቸው 14 ሴቶች ጋር ቃለ መጠይቅ አድርጐ ነበር። አብዛኞቹ ተሳታፊዎች በደረሰባቸው ጥቃት ምክንያት ዝምታን እንደመረጡና ኢንተርኔት ላይም ሆነ ከኢንተርኔት ውጪ ካሉ ማህበራዊ እንቅስቃሴ ላይ ራሳቸውን ማግለላቸውን ገልፀዋል ።

ሴቶችና ልጃገረዶችን በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ካደረጉ ጥቃቶች መካከል በሁሉም ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ንቁና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያበረታታል። ከላይ እንደተገለፀው በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ከታሪካዊ፣ ሀይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ አመለካከቶች የሚመነጩ ናቸው። በመሆኑም በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ስላደረጉ ጥቃቶች አይነትና መፈፀሚያ መድረክ ማጥናት ችግሩ ላይ ያነጣጠሩና ውጤታማ የሆኑ የመፍትሔ ፖሊሲዎችን ለመቅረፅ ያግዛል ።




*ምስል3፡ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች የሚያበረክተውን የመገለል ዑደት ለማሳየት ሥዕላዊ መግለጫ።*

## የፕሮጀክቱ ግቦች

- ኢትዮጵያ ውስጥ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ያለውን ማስረጃ ማጠናከር
- የመንግስት ተቋማት ፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ፣ የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎችና ማህበረሰቡ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ስላደረጉ ጥቃቶች ያላቸውን ግንዛቤ ማሻሻል
- በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን በመከላከል ዙሪያ ለሚሰሩ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የመንግስት ተቋማት ተግባራዊ ምክረ-ሀሳቦችን ማቅረብ

## የጥናቱ ጥያቄዎች

- **መልክ (አይነትና አዉድ)** የትኛዉ አይነት ፆታዊ የጥላቻ ንግግር በሰፊዉ ይታያል? የጥላቻ ንግግሮቹ አወድ ምን አይነት ናቸው? የጥላቻ ንግግሮች ከፆታ ልዩነት አንፃር እንዴት ይታያሉ?
- **ተደራራቢ ጥቃቶች** የጥላቻ ንግግሮች ከፆታ በተጨማሪ ሀይማኖትና ብሔርን የመሰሰሉ ሌሎች ማንነቶችን ኢላማ ሲያደርጉ እንዴት ይለያሉ?

- **መድረክ** ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች በማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች መሀል ልዩነት አላቸዉ?

## የጥናቱ ወሰን

ሲ.አይ.አር እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ከኤክስ (በቀድሞ ስሙ ቲውተር)፣ ከቴሌግራምና ፌስቡክ ላይ ይዘቶችን በመውሰድ መርምሯል። ይህም የጥቃቶቹን መልክና መድረክ ከመጠቀሙ በተጨማሪ የተደራራቢ ጥቃቶችን (የጥላቻ ንግግር ብዙ ማንነቶችን በአንድ ጊዜ ሲያጠቃ) አውድ ለማየት አስችሏል። ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ያለውን ሰፊ መረጃ መሰብሰብና መተንትን ለማስቻል በቴክኖሎጂ ከታገዙና ፆታን መሠረት ካደረጉ ጥቃቶች ውስጥ የጥናቱን ትኩረት ፆታን መሠረት ባደረገ ጥላቻ ንግግር ላይ ማድረግ አስፈልጓል። ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነት እንዲኖረው በማሰብ የጥላቻ ንግግር የኢትዮጵያ መንግስት የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ባወጣው አዋጅ መሠረት ተተርጉሟል።[7] ወደ ፊት የሚደረጉ ጥናቶች ጥላቻን ለማራመድ ምስሎችን በመጠቀም፣ ለበቀል በሚለቀቁ ወሲባዊ ምስሎችና በታዋቂ ሠዎች ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች ዙሪያ ሊያተኩሩ ይችላሉ።

ሲ.አይ.አር እ.ኤ.አ ከግንቦት 2023 ጀምሮ በጥላቻ ንግግር ቃላቶች ዙሪያ ጥናት አድርጓል። እ.ኤ.አ ሐምሌ 2023 ላይ አዲስ አበባ በመምጣትና ከሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮችና ሰብዓዊ መብት ተቋማት ጋር ውይይቶች በማካሄድ ከአማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች የተወጣጡ 2000 ጥላቻ አዘል ቃላቶችን መርጧል።

እ.ኤ.አ በነሀሴ 2023 ሲ.አይ.አር ቁልፍ ቃላትን የሚያዘምዱና የጥላቻ ንግግሮችን የሚለዩ ሞዴሎችን በመጠቀም ሶስቱ ማህበራዊ ድህረ-ገፆች ላይ ካሉ ልጥፎች ላይ ናሙና ወስዷል። አንድ የአጥኚዎች/ባለሙያዎች ስብስብ ከኤክስና ቴሌግራም ላይ የተገኘውን መረጃ በሶስት መስፈረቶች ማለትም በጥቃቶቹ ኢላማ፣ አይነትና አውድ ለይቶታል። ከፆታ ውጪ ባሉ ሌሎች ማንነቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን የማጥናት አስፈላጊነት በቀድሞ ጥናት ላይ ስለታየ ይህ ጥናት በኢትዮጵያ መንግስት ባወጣው የጥላቻ ንግግር አዋጅ ላይ ህጋዊ ከለላ ባገኙ ማንነቶች (አካል ጉዳተኝነት፣ ብሔር፣ ፆታ፣ ዘርና ሀይማኖት)[8] ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመመርመር ጥናቱን አስፍቷል።

ሲ.አይ.አር እ.ኤ.አ ታህሳስ 2023 መጨረሻ ላይ አዲስ አበባ ውስጥ ባካሄደው አውደ ጥናት ላይ የጥናቱን የመጀመሪያ ዙር ግኝቶች ለባለድርሻ አካላት አጋርቷል። ፌስቡክ በማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፁ ላይ ባለው የተለየ ፖሊሲ ምክያት ከመተግበሪያው ላይ መረጃዎችን ለማግኘት ጊዜ በመውሰዱ ከፌስቡክ ላይ የተገኙ መረጃዎች የተለዩት እ.ኤ.አ በታህሳስ 2023 ነበር። እ.ኤ.አ በጥር 2024 የተገኙት መረጃዎች ከዚህኛው ጥናት ጋር ከተዋሃዱ በኋላ እ.ኤ.አ በየካቲት 2024 ጥናቱ ለባለድርሻ አካላት ቀርቧል።

---

[7] የአዋጅ ቁጥር 1185/2020, በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ላይ እንደሚታየው (እ.ኤ.አ 2020): https://ethionab.org/wp-content/uploads/2022/09/1185_2020_HATE_SPEECH_AND_DISINFORMATION_PREVENTION_AND_SUPPRESSION_PROCLAMATION_.pdf

[8] የአዋጅ ቁጥር 1185/2020, በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ላይ እንደሚታየው (እ.ኤ.አ 2020)፡ https://ethionab.org/wp-content/uploads/2022/09/1185_2020_HATE_SPEECH_AND_DISINFORMATION_PREVENTION_AND_SUPPRESSION_PROCLAMATION_.pdf

## 3. የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ጥናት ላይ ሲ.አይ.አር በኢትዮጵያ ማህበራዊ ትስስር ገፆች ላይ በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚደርሱትን የተለያዩ የጥላቻ ንግግሮች አውድና የጥቃቶቹን ኢላማ አጥንቷል። በዚህ ጥናት ውስጥ የጥላቻ ንግግር 'አይነት' የጥቃቱን መፈፀሚያ ዘዴን ሲያሳይ (እንደ 'ዛቻ')፣ አውድ ደግሞ ከጥቃቱ ጀርባ ያለውን ስሜትና የቋንቋ አጠቃቀም (እንደ 'ፌዝ') ያሳያል። በዚህ ጥናት ላይ የተካተቱ የጥቃት አይነቶችና አውዶች ሀሳባዊ ማዕቀፍ ከታች በክፍል 3.1 ላይ ተያይዟል። ሀሳባዊ ማዕቀፉ፣ የመረጃ አተረጓጎም ፕሮቶኮልን ጨምሮ ሰፊው የጥናቱን ዘዴ የሚያካትት ስለሆነ የጥናቱ ውጤቶችን ለመተርጎም አስፈላጊ ነው። መረጃዎቹን በአይነታቸው የመደቡት ባለሙያዎች አንድን ይዘት ጥላቻ ንግግር ብለው የሰየሙት የጥቃቱ አይነትና የጥቃቱ ኢላማ (የህግ ከለላ ያለው ቡድን ለምሳሌ ፆታ) በግልፅ ሲታወቅ ብቻ ነው።

በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች መካከል የተገኘውን ውጤት ለማወዳደር በማሰብ ሲ.አይ.አር በሶስቱ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ የተጠቀመው የጥናት ዘዴ ተመሳሳይ ነው። *'Natural Language Processing'* የጥናቱ ዘዴ ዋና አካል ሲሆን ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያለውን ፅሁፍ ለመተንተንና ለመተርጎም አግዟል። ይህም የቃላት ስብስቦችን ማዘጋጀት፣ መረጃዎችን ከማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ መሰብሰብ፣ መረጃዎቹ ከመተርጎማቸው በፊት ማዘጋጀት (ድግግሞሾችን ማስቀረትና የይዘቶችን ሚስጥራዊነት መጠበቅ) ያካተተ ነበር። ሲ.አይ.አር *'Natural language processing'*ን በከፊል በመጠቀም ጥላቻ ንግግሮችን መለየት በመቻሉ የሰው ሀይልን መቀነስ ተችሏል። በመጨረሻም ሲ.አይ.አር *'Natural language processing'*ን በሰው ሃይል ለተሰራው የመረጃ ትርጓሜ ተጠቅሞበታል። እነዚህ ቅደም ተከተሎች በሚቀጥለው ክፍል ላይ ተዘርዝረዋል።

የዚህ ጥናት ዘዴ በሙያው ላይ ትልቅ ስም ባላቸው ምሁራን የተገመገመ ሲሆን "ሪሶርስ ፎር አፍሪካን እንዲጅነስ ላንጉጅስ (Resource for African Indigenous Languages)" በተባለው ትምህርታዊ ህትመት ላይ ይቀርባል።[9]

### ሃሳባዊ ማዕቀፍ

ኢትዮጵያ ውስጥ በኢንተርኔት ላይ ስላለው ፆታን መሠረት ያደረገ ጥላቻ ንግግር ለማጥናት ሲ.አይ.አር የጥላቻ ንግግር ቁልፍ መገለጫዎችን የሚያሳይ ሃሳባዊ ማዕቀፍ አዘጋጅቷል። እነዚህም የጥቃቱ ኢላማ፣ አይነትና አውድ ናቸው። አንድ ይዘት የጥላቻ ንግግር ለመባል ከኢላማ በተጨማሪ የጥቃቱ 'አይነት' ግልፅ መሆን አለበት። ሲ.አይ.አር ትንተናውን ጥልቅ ለማድረግ በማሰብ የጥቀቶቹን 'አውድ' በትንተና ውስጥ አካቷል።

ሲ.አይ.አር የኢትዮጵያ መንግስት ባረቀቀው የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ መከላከያና መቆጣጠሪያ አዋጅ ላይ ህጋዊ ከለላ ያገኙ ቡድኖችን እንደ ጥቃት ኢላማ አድርጎ ወስዷል።[10] ከፆታ ውጪ ሌሎች ማንነቶችም ጭምር የጥላቻ ንግግር ሰለባ ስለሚሆኑ ይህ ሃሳባዊ መዕቀፍ በሌሎቹ ማንነቶች ላይ (አካል ጉዳተኝነት፣ ብሔር፣ ፆታ፣ ዘርና ሃይማኖት)

---


[9] 'Resources for African Indigenous Languages' (እ.ኤ.አ 2024) በዚህ ማስፈንጠሪያ ይገኛል: https://sadilar.org/en/the-fifth-workshop-on-resources-for-african-indigenous-languages-rail/

[10] የአዋጅ ቁጥር 1185/2020, በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ላይ እንደሚታየው (እ.ኤ.አ 2020): https://ethionab.org/wp-content/uploads/2022/09/1185_2020_HATE_SPEECH_AND_DISINFORMATION_PREVENTION_AND_SUPPRESSION_PROCLAMATION_.pdf

ላይ የሚደርሱትን የጥላቻ ንግግሮችንም አካቷል። ይህም የጥላቻ ንግግሮች የአንድን ሰው የተለያየ ማንነቶች በተመሳሳይ ጊዜ ኢላማ ሲያደርጉ ያለውን ሁኔታ ለማሳየት አስችሏል።

በዚህ ጥናት ላይ የጥላቻ ንግግር 'አይነት' ሲባል ጥቃቱ የሚደርስበትን ዘዴ (እንደ 'ዛቻ') ሲያመለክት 'አውድ' ደግሞ ከጥላቻ ንግግሩ ጀርባ ያለውን ስሜትና የቋንቋ አጠቃቀም (እንደ 'አሽሙር') ያመለክታል። የዚህ አጠቃላይ ይዘት በሚቀጥለው ምስል ላይ ተካቷል።

የጥላቻ ንግግርን መነሻ መረዳት ጥላቻ ንግግሮች እንዴት ሊለያዩ እደሚችሉ (በኢላማ፣ በአይነትና በአውድ) ለማወቅና ችግሩ ላይ ያነጣጠረ መፍትሄ ለመስጠት ቁልፍ ሚና ይጫወታል።




*ምስል4: የጥናቱን ዲዛይንና የትርጓሜ ሂደት የሚያሳይ የሲ.አይ.አር ሃሳባዊ ማዕቀፍ*

## ቃላትን ማሰባሰብ


ሲ.አይ.አር ፆታን፣ ብሔርንና ሀይማኖትን ኢላማ ያደረጉ 2058 የጥላቻ ንግግር ቃላትን በአራት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ፣ በአፋን ኦሮሞ፣ በትግርኛና በእንግሊዘኛ አዘጋጅቷል። ይህ የቃላቶች ስብስብ በኢትዮጵያ እስካሁን ካሉት ስብስቦች አንፃር ሁሉን አካታች ነው ብሎ ሲ.አይ.አር  ያምናል። ምስል 3 በእያንዳንዱ ማንነት ዙሪያ የተመረጡትን የቁልፍ ቃላት ብዛት ያሳያል።

የቃላቶቹ ስብስብ የተዘጋጀው ከዚህ በፊት የነበሩ የቃላት ስብስቦች በማየትና በማጥራት፣[11] በመጀመሪያው ጥናት ከተዘጋጁትና በከፊል ከተዋቀሩት ቃለመጠይቆች ላይ ቃላቶችን በመውሰድ[12] እና እ.ኤ.አ በሐምሌ 2023  አዲስ አበባ ውስጥ  በተካሄደው ስብሰባ ላይ ቃላቶችን በመምረጥ ነበር። በስብሰባው ላይ የተሳተፈው የባለሙያዎች ስብስብ ከተለያዩ የሲቪል ማህበራት፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች እና ከሴቶች መብት ተሟጋች ቡድኖች የተወጣጡ 22 ግለሰቦችን ያካተተ ነበር። በዚህ ውይይት ላይ ሲ.አይ.አር የመጀመሪያውን ጥናት ውጤት በማቅረብ በአራቱም ቋንቋዎች ጥላቻ ንግግርን ባዘሉ ቃላቶች ዙሪያ ውይይት ተደርጓል። በዚህም ውይይት አዳዲስ የጥላቻ ንግግር የያዙ ቁልፍ ቃላቶች ከመገኘታቸውም በተጨማሪ የተወሰኑ ቃላቶች ለምን የጥላቻ ንግግር እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል። ይህ ውይይት የቃላቶቹን ስብስብ ለማዘጋጀት መመሪያ  ሆኗል። የፖለቲካ  አመለካከቶች  በኢትዮጵያ  መንግስት የጥላቻ ንግግር ትርጉም ውስጥ  ህጋዊ  ከለላ ስላላገኙና ሌሎች ክፍሎች ውስጥ ሊመደቡ የማይችሉ ብዙ የጥላቻ ንግግር ቃላቶች ስለተነሱ 'ለሌሎች ቃላቶች' እና 'ለፖለቲካ' ጥላቻዎች ተጨማሪ ክፍሎች ተካተው ነበር።

የቃላቶችን ስብስብ የያዘ የመጀመሪያ ረቂቅ ለሲ.አይ.አር አጋሮች፣ ለባድርሻ አካላት እና አዲስ አበባ ውስጥ የተካሄደውን ስብሰባ ለታደሙ ተሳታፊዎች በማጋራት ግብረመልስ ተሰብስቧል። በዚህም ጊዜ አንዳንድ ቃላቶች ለብቻቸው የጥላቻ ንግግርን ስለማያመለክቱ ከጥላቻ ንግግር ስር መመደባቸው ግርታን ፈጥሮ ነበር። እነዚህ ቃላቶች በራሳቸው ጥላቻ ንግግርን ባይወክሉም  የጥላቻ ንግግር ይዘቶችን ከማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ለመለየት እንደሚጠቅሙና የተገኙት ይዘቶች በመጨረሻም በባለሙያዎች ጥላቻ ንግግር መሆናቸውና አለመሆናቸው እንደሚለይ ሲ.አይ.አር አስረድቷል። አንድ ቃል በአንድ ማህበራዊ ይዘት ውስጥ በመገኘቱ ብቻ ይዘቱ የጥላቻ ንግግር ነው ማለት አይቻልም።

ግብረ መልሶቹ ከተካተቱ፣ ስህተቶች ከታረሙና  ድግግሞሾች  ከተወገዱ  በኋላ የአማርኛ፣ የአፋን ኦሮሞ፣ የትግርኛና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ክህሎት ያላቸው ሶስት የማህበራዊ ሚዲያ ባለሙያዎች የተመረጡትን ቃላቶች ለጥናቱ በተመረጡ 4 ቋንቋዎች ስር በትክክል መመደባቸውን አረጋግጠዋል። ይህ ጥናት ፆታን መሰረት ባደረገ ጥላቻ ንግግር  ላይ እንደማተኮሩ በፆታ ላይ ያተኮሩት  ቃላቶች  ሌሎች ማንነት ላይ ካተኮሩት ቃላቶች የበለጠ ነበር።  ሆኖም ግን በሌሎች ማንነቶች ዙሪያ የተሰበሰቡት ቃላቶች ከዚህ  በፊት ከተሰሩ ጥናቶች ጋር ሲወዳደር ሁሉን አቀፍ ነው።

[11] See section 8, bibliography, for a full list of the resources consulted.
[12] CIR (2023) Silenced, shamed and threatened: the online abuse of women and girls who participate in Ethiopian public life.




*ምስል 5: በመረጃ አሰባሰብ ወቅት የነበረውን ጥላቻ-አዘል ቃላት ስብጥር የሚያሳዩ ግራፎች*

## የመረጃ አሰባሰብ

ሲ.አይ.አር ኤክስን፣ ቴሌግራምንና ፌስቡክን ለዚህ ጥናት መርጧል። እነዚህ ሶስቱ የማህበራዊ ሚዲያ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ፣ ሴቶች በዋነኝነት ጥቃት የሚደርስባቸዉ መድረኮች እንደሆኑ በሲ.አይ.አር የመጀመሪያ ጥናት ላይ በቃለ መጠይቁ ሰኣት ተሳታፊዎች ገልፀዋል። እ.ኤ.አ 2023 'ስታቲስታ' የተባለዉ ድርጅት ስለ ማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ቁጥር ባወጣዉ መረጃ ፌስቡክ ኢትዮጵያ ዉስጥ በ6.5 ሚሊዮን ተጠቃሚዎች የመጀመሪያዉን ደረጃ ሲይዝ ሜሴንጀር፣ ሊንክዲንና ኢንስተግራም ቀጣዮቹን ደረጃ ይይዛሉ።[13] እ.ኤ.አ በ2023 መጀመሪያ ላይ የቴሌግራም መተግበሪያ በአንድሮይድ (እትዮጲያ ውስጥ እጅጉን የተለመደው የስማርትፎን ኦፕሬቲንግ ሲስተም[14]) ስልኮች ላይ በመጫን ቁጥር አንድ ማህበራዊ መተግበሪያ ነበር።[15] በቴሌግራም ላይ በሚፈፀሙ ጥቃቶች ዙሪያ ያለዉ የጥናት እጥረት በጉዳዩ ላለዉ ተዛማጅ ፅሁፍ እጥረት ምክንያት ነዉ።

ኤክስ፣ ፌስቡክና ቴሌግራም ባላቸዉ ፅሁፋዊ ይዘት ምክንያት ጥናቱ በሶስቱም ማህበራዊ ትስስር ደህረ ገፆች ላይ የተጠቀመዉ ዘዴ ተመሳሳይ ነዉ። ሲ.አይ.አር በዩቲዩብና ቲክቶክ ላይ ያለዉን ፆታዊ ጥላቻ ንግግር ለማየት ቢፈልግም የእነዚህ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ይዘት የቪዲዮ መሆኑ ሌላ አይነት የጥናት ዘዴ አስፈልጓል። ወደፊት የሚሰሩ ጥናቶች በእነዚህ መድረኮች ላይ አተኩረዉ ሊሰሩ ይችላሉ።

በሶስቱ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ህግና ደንብ ልዩነት ምክንያት ከሶስቱ መድረኮች ላይ መረጃ የተሰበሰበበት መንገድ የተለያየ ነበር። በዚህም ምክንያት ከእያንዳንዱ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ የተሰባሰበዉን የጥላቻ ንግግር

[13] Statista (2023) Social media users by Platform in Ethiopia, Available at: https://www.statista.com/statistics/1312554/social-media-users-by-platform-in-ethiopia/
[14] StatCounter (2023) Mobile Operating System Market Share Ethiopia, Available at: https://gs.statcounter.com/os-market-share/mobile/ethiopia
[15] This was reported by Addis insight, citing data from the Google Play store: Addis Insight (2022) Available at: https://addisinsight.net/why-telegram-is-so-popular-in-ethiopia/; however, this is consistent with reporting from previous years, for example, see: Quartz (2018) Available at: https://qz.com/africa/1214381/in-a-continent-dominated-by-whatsapp-ethiopia-says-yes-to-telegram

ብዛት በጥሬው ማወዳደር ስለማይቻል ቁጥሮቹ ብቻቸዉን ለጥናቱ ዉጤት አስፈላጊ አይደሉም። ይልቁንም ከአጠቃላዩ የጥላቻ ንግግር ስብስብ ዉስጥ የጥቃቶቹ አይነት፣ ኢላማና አውድ ማጥናት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

### 3.3.1. ኤክስ (በቀድሞ ስሙ ትዊተር)

ሲ.አይ.አር ከኤክስ ላይ መረጃዎችን ለመሰብሰብ **ሜልትወተር (Meltwater)**[16] የተባለዉን የማህበራዊ ሚዲያ መተንተኛ መተግበሪያ ተጠቅሟል። ሜልትወተር ቁልፍ ቃላትን በማስገባት ከፍለጋዉ ቀን 18 ወራቶች ወደኋላ ድረስ ያሉ የትዊተር ልጥፎችን በማሰባሰብ ዉጤቶችን ያመጣል። ሜልትወተር የአንድን ልጥፍ ማስፈንጠሪያ፣ ይዘት፣ የፀሃፊዉን ስምና መለያ ስም፣ የተፃፈበት መሳሪያ (ስልክ፣ ኮምፒዉተር፣ አንድሮይድ፣ አይፎን)፣ የፀሃፊዉን ገፅ ማስፈንጠሪያ፣ የፀሃፊዉን ተከታዮች ቁጥር፣ ፀሃፊዉ የሚከተላቸዉ የሰዎች ቁጥር፣ የፅሁፉ እይታ ቁጥር፣ በፅሁፍ ላይ ያሉ አስተያየቶች፣ ልጥፉን ያልወደደዱት ሰዎች ቁጥር፣ ፅሁፉ ምን ያህል እንደተጋራ፣ በፅሁፍ ዙሪያ ያሉ ምላሾችና ፀሃፊዉ በትዊተር የተረጋገጠ መሆኑን ያሳያል።

ሰንጠረዥ1 ከኤክስ ላይ የተወሰዱትን ልጥፎች ቁጥር ያሳያል። የሲ.አይ.አር አጥኚዎች የእንግሊዘኛ ልጥፎችን ሲወስዱ በኢትዮጵያ ዉስጥ የተፃፉትን ብቻ መርጠዋል።

### 3.3.2. ቴሌግራም

ሲ.አይ.አር በቴሌግራም ላይ መረጃዎችን ለማግኘት ዋናዉን የቴሌግራም መተግበሪያ ተጠቅሟል።[17] በቴሌግራም ላይ መረጃዎችን ማግኘት የሚቻለዉ የቴሌግራም ጣቢያዎቹ በመቀላቀል ብቻ ስለሆነ የማህበራዊ ሚዲያ ባለሙያዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ ትልቅና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ የቴሌግራም ገፆችን እንዲመርጡ ተደርጓል። ሲ.አይ.አር የስነምግባር መመሪያዎችን በማክበር ለህዝብ ክፍት የሆኑ ጣቢያዎችን ብቻ ተጠቅሟል።

310 የሚሆኑ የቴሌግራም ጣቢያዎች ከተመረጡ በኋላ 285ቱን በመቀላቀል ለዚህ ጥንት መረጃ መሰብሰብ ተችሏል። በቴሌግራም ላይ ከተገኙት ልጥፎች ጋር የለጣፊዎቹን ልዩ ስምና መለያ ቁጥር፣ የልጥፉን ይዘት፣ የልጥፉን ማስፈንጠሪያ፣ የጣቢያዉን መለያና የለጣፊዉን ሙሉ ስም ማግኘት ተችሏል። ሰንጠረዥ 1 ከቴሌግራም ላይ የተገኙትን ልጥፎች ቁጥር ያሳያል።

### 3.3.3. ፌስቡክ

ፌስቡክ ከኤክስና ቴሌግራም ባለዉ የተለየ የመረጃ አሰባሰብ ፖሊሲ ምክንያት ሲ.አይ.አር ሜልትወተር የተባለዉን መተግበሪያ መረጃ ለመሰብሰብ አልተጠቀመም። ይልቁንም ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉ የማህበራዊ ሚዲያ ባለሙያዎች፣ ታዋቂና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ የፌስቡክ ግሩፖችን እንዲመርጡ በማድረግ ከ300 በላይ ግሮፖች ተገኝተዋል። ከፌስቡክ

[16] Meltwater, Available at: https://explore.meltwater.com/uk/all-in-one
[17] Other scraping tools could be used, such as Tom Jarvis' 'Telegram Snowball Sampling' tool, available on GitHub. Available at: https://github.com/thomasjjj/Telegram-Snowball-Sampling

ላይ የተገኘዉ መረጃ የልጥፉን ማስፈንጠሪያ፣ የለጣፊዉን ልዩ ስምና መለያ ቁጥር ፣ ልጥፉ የተጋራበት መጠን፣ ልጥፉ የተወደደበት (ላይክ የተደረገበት) ቁጥር እና የእይታ ቁጥሩን ያካተተ ነዉ።

ይህ የተለየ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ ለትንተና የተመረጡትን ልጥፎች ቁጥር አሳንሷል። በሌሎች ሁለቱ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ተግባራዊ የተደረገዉ ማጣሪያ ዘዴ እዚህኛዉ ላይ ባለመተግበሩ ምክንያት የተገኙት አውነተኛ የጥላቻ ንግግሮች ቁጥር ማነስ በጥናቱ ዉጤት ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል።

## የመረጃ አዘገጃጀት

### 3.4.1. የመረጃ ቅድመ ዝግጅት

የመረጃ ቅድመ ዝግጅት በማንኛዉም *'Natural language processing'* ዘዴ ዉስጥ አስፈላጊ ደረጃ ነዉ። ይህም መረጃዉን ማፅዳትና ለትንተና ብቁ እንዲሆኑ ማደራጀትን ያካተተ ነዉ። ይህ የመረጃ ቅድመ ዝግጅት የቋንቋ ሞዴሎችን ጥራትና ታማኝነት ከመጨመር በተጨማሪ ከፅሁፎች ላይ ትርጉም ያላቸዉ ሀሳቦችን ለማግኘት ቁልፍ ነዉ። ከዚህ በታች በአራቱ ቋንቋዎች በሰበሰበዉ መረጃ ላይ የተሰራዉ የመረጃ ቅድመ ዝግጅት ይታያል።

**ፅሁፎችን ማጥራት:**

ከማህበራዊ ሚዲያ ላይ የሚወሰዱ ፅሁፎች አብዛኛዉን ግዜ ለመተንተንና ለመተርጎም እንቅፋት የሚሆኑ አላስፈላጊ መረጃዎችን ይይዛሉ። መረጃ ማጥራት የሚከተሉትን ያካተተ ነበር።

i. የኢንተርኔት ማሰሻ መተግበሪያዎች የኢንተርኔት መረጃዎችን እንዴት ማሳየት እንዳለባቸዉ የሚያግዙ መለያዎችንና (HTML tags) እና የተለዩ ፊደላቶችን ማስወገድ። እነዚህ መለያዎችና የተለያዩ ፊደላት የአንድን ድህረ-ገፅና ፅሁፎቹን መልክ ለመቀየር እንጂ ለጥናቱ የተዘጋጁ ፅሁፎችን ለመተርጎም ጠቃሚ አይደሉም።

ii. .በእንግሊዘኛ ያሉትን አብይ ፊደላት ወደ ትናንሽ ፊደላት (Capital letters to Small letters) በመለወጥ ቃላቶቹ ተመሳሳይ ይዘት እንዲኖራቸዉ ማድረግ

iii. ስርዓተ ነጥቦችን ማስወገድ ወይም መተካት

የሚከተሉት መረጃን የማፅዳት ስራዎች በእንግሊዘኛ ቋንቋ በተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ ብቻ የተሰሩ ናቸዉ። ሲ.አይ.አር ይህን ያከናወነው ፅሁፋዊ ልጥፎቹን ጥላቻ ወይም ጥላቻ ያልሆኑ ብለው ለሚለዩት ሞዴሎች እንዲመች በማሰብ ነው

i. ቁጥሮችን፣ ቀኖችንና ሌሎች ፅሁፍ ነክ ያልሆኑ መረጃዎችን ማስወገድ
ii. ማያያዘዣ ቃላቶችን (“and” “the” “in” የመሳሰሉና ለብቻቸዉ ትርጉም የሌላቸዉ) መቀነስ
iii. ምህፃረ ቃላትን መተንተን። ምህፃረ ቃላት በአብዛኛዉ ጎጂ የሆነ መልዕክቶችን በድብቅ የማስተላለፊያ መንገድ ስለሆኑ እነዚህ ምህፃረ ቃላቶች መተንተን የጥላቻ ንግግሮችን ለመለየት ይረዳናል።

## ድግግሞሾች ማስወገድ

ሲ.አይ.አር ፅሁፎቹን ካጣራ በኋላ ድግግሞሾቹን ለይቶ አስወግዷል። ድግግሞሽ ስታቲስቲካዊ ትንተናዉን ስለሚያዛባ ይህ መደረጉ ለጥናቱ አስፈላጊ ነዉ። ይህ ከተደረገ በኋላ ከኤክስ ላይ የተገኘዉ የመረጃ ስብስብ ከፍተኛ መቀነስ አሳይቶ ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት ብዙ ቁልፍ ቃላቶች በአንድ ልጥፍ ላይ ስለሚገኙና እነዚህን ቁልፍ ቃላቶች ፈልገን መረጃ በወሰድን ቁጥር ተመሳሳይ ልጥፍ ስለሚካተት ነዉ።

ቴሌግራም ላይ በድግግሞሽ ምክንያት የተወገዱት አብዛኛዎቹ ልጥፎች *"ይህ ግሩፕ የአካባቢዉን ህግ ስለጣሰ ማየት አይችሉም"*የሚሉ ነበሩ። ከዚህ በታች የተቀመጠዉ ሰንጠረዥ ከላይ በተገለፀዉ ምክንያት ከቴሌግራም ላይ የተወገዱ የልጥፍ ቁጥሮችን ያሳያል። እነዚህ ልጥፎች ከመወገዳቸዉ በፊት ሲ.አይ.አር ቁልፍ ቃል ብሎ የያዛቸዉን ቃላቶች የያዙ ነበር።

| | የተወገዱት ልጥፎች ቁጥር |
|---|---|
| እንግሊዝኛ | 94,261,111 |
| አማርኛ | 43,356 |
| አፋን ኦሮሞ | 301,460 |
| ትግርኛ | 34,508 |

*ሰንጠረዥ 1: ከቴሌግራም ግሩፖች ላይ የአካባቢውን ደንብ በመጣስ የተወገዱ ልጥፎች ቁጥር.*

ፌስቡክ ላይ በነበረዉ የተለየ መረጃ አሰባሰብ ዘዴ ምክንያት ድግግሞሽ አልነበረም። ፌስቡክም ሆነ ኤክስ "የአካባቢውን ህግ በመጣስ" በሚል የተተኩ ልጥፎች አልነበራቸዉም። ይህም የሆነዉ ሁለቱም የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች የአካባቢውን ህግ የጣሱ ልጥፎችን ሙሉ ለሙሉ ስለሚያስወግዱ ሊሆን ይችላሉ።

### መረጃዎችን ስም አልባ ማድረግ

ሲ.አይ.አር የስነምግባር መስፈርቶችን ለማሟላት ለዚህ ጥናትና ትንተና ልጥፎቻቸዉን እንደመረጃነት የተወሰዱባቸዉን ግለሰቦች ልዩ ስም ደብቋል። ይህም ልዩ ስማቸዉን n'@username' በመተካት የተከናወነ ነዉ።

## 3.4.2. መረጃዎችን የጥላቻ ወይም የጥላቻ ያልሆኑ/ሰላማዊ ብሎ መመደብ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በማህበራዊ ሚዲያ ልጥፎች ላይ ያለዉን የጥላቻ ንግግር መለየትና ማጥናት ነዉ።በተለምዶ እነዚህን ልጥፎች መለየት በእጅ የሚደረግ ግምገማ ሂደትን ያካትታል፣ እያንዳንዱ ልጥፍ የጥላቻ ንግግር እንደያዘ ለማወቅ በባለሙያ የሚገመገምበት ነው።

ሲ.አይ.አር ይህን ሂደት ለማፋጠንና ባለሙያዎች የጥላቻ ንግግርን ለማግኘት ማየት ያለባቸዉን ጤናማ ልጥፎች ለመቀነስ አዉቶማቲክ የሆነ መረጃን የመለያ ዘዴ አስተዋዉቋል። በዚህ ዘዴ የጥላቻ ንግግር ተብለዉ የተመደቡት

ልጥፎች ወደ ቀጣዩ የትንተና ሂደት አልፈዋል። ይህ አካሄድ የጥላቻ ንግግር አይዙም ተብለዉ የሚታሰቡ ልጥፎች ያስወግዳል።

መገንዘብ ያለብን ትግርኛና አፋን ኦሮሞን ተረድቶ የጥላቻ ንግግሮችን የሚለይ ቀድሞ የተዘጋጀ ሞዴል ስላልነበረ ከላይ የተጠቀሰዉ ዘዴ በአማርኛና እንግሊዘኛ ልጥፎች ላይ ብቻ ተተግብሯል። በዚህም ምክንያት የአማርኛና የእንግሊዘኛ ልጥፎች ከትግርኛና ከአፋን ኦሮሞ ልጥፎች አንፃር ተጨማሪ የማጣራት ሂደት አልፈዋል።

### 3.4.3. ለቀጣይ ትንተናዎች የመረጃ ናሙና መረጣ

ሲ.አይ.አር ከላይ የተጠቀሱትን የመረጃ ማሰባሰብ ሂደቶች ካጠናቀቀ በኋላ በአስር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ልጥፎችን ማግኘት ችሏል (በሰንጠረዥ 2 ላይ እንደሚታየው)። ድግግሞሽን ማስወገድና አጭር የሆኑ ልጥፎች መቀነስን ያካተተ ሰፊ የሆነ የመረጃ ቅድመ ዝግጅት ከተካሄደ በኋላ እንኳን ከ5ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ልጥፎች ቀርተዋል።

መረጃዎች በሰው እጅ ለመለየት ካለው የሰው ሀይል አንፃር ሲ.አይ.አር የተወሰኑ መረጃዎችን በዕጣ መርጦ ለቀጣይ ትንተና አዘጋጅቷል። ሰንጠረዥ 2 ለቀጣይ ትንተና የተመረጡ ልጥፎችን ቁጥር ያሳያል።

ሲ.አይ.አር መረጃዎችን ከሶስት ማህበራዊ ሚዲያዎች በአራት ቋንቋዎች ሰብስቧል። ሲ.አይ.አር በምርጫ ሂደት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ አድሎአዊ ጉዳዮችን ለመቅረፍ በማሰብ ወደ ቀጣይ ትንተና የሚሸጋገሩትን ልጥፎች በዕጣ መርጧል።

### 3.4.4. በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች የመረጃ አዘገጃጀት ሂደት በቁጥር

የተለያየ አይነት የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ በመኖሩ ምክንያት ከኤክስ፣ ቴሌግራምና ፌስቡክ በተሰበሰቡ ልጥፎች መሃል የቁጥር ልዩነት አለ። ለምስሌ ከፌስቡክ ላይ 7230 ልጥፎችን ብቻ መሰብሰብ ሲቻል ከኤክስ 865,224 ከቴሌግራም ላይ ደግሞ 326,471,094 ልጥፎችን መሰብሰብ ተችሏል።

የመረጃ ቅድመ ዝግጅት ከተካሄደ በኋላ ከኤክስ የተገኙት ልጥፎች ወደ 527,522 (መጀመሪያ ከተሰበሰበው 60.97 ከመቶ) ቀንሷል። የቴሌግራም ልጥፎች ቁጥር ደግሞ ወደ 906.471 (መጀመሪያ ከተሰበሰበው 0.28 ከመቶ) ወርዷል። በመጨረሻም የፌስቡክ ልጥፎች ቁጥር ምንም ለውጥ አላጣም። (ለበለጠ ማብራያ ክፍል 3.3.1 ይመልከቱ)።

በመቀጠልም ሲ.አይ.አር የሰው ሰራሽ አስተምሮትን (Machine Learning) በመጠቀም የጥላቻ ይዘት የሌላቸው ልጥፎችን አውጥቷል። ይህ የሰው ሰራሽ አስተምሮት ሞደል ከቴሌግራም ይልቅ ከፌስቡክና ኤክስ ላይ ብዙ የጥላቻ ይዘት ያላቸውን ልጥፎች መለየት ችሏል። ይህም ልዩነት የመጣው ሞዴሉ ኤክስ ላይ ያሉ ፅሁፎች ለመለየት የሰለጠነ በመሆኑና ፌስቡክና ቴሌግራም ላይ ያሉት አፃፃፍ ስልቶች ከኤክስ ለየት ስለሚሉ ነው። ለምሳሌ የቴሌግራም ልጥፎች ረዘም ያሉና ከኤክስ ልጥፎች ጋር ሲወዳደሩ ምህፃረ ቃል የበዛባቸው ናቸው። ከላይ እንደተጠቀሰው ይህ ሞዴል በእንግሊዘኛ እና አማርኛ ቋንቋዎች ብቻ ስለተሰራ በአፋን ኦሮሞና ትግርኛ ልጥፎች ላይ አልተተገበረም።

በመጨረሻም ሲ.አይ.አር 2634 የኤክስ ልጥፎችን፣ 2170 የቴሌግራም ልጥፎችን እና 2264 የፌስቡክ ልጥፎችን በዕጣ መርጧል።

| | ኤክስ | ቴሌግራም | ፌስቡክ |
|---|---|---|---|
| የተሰበሰቡ ልጥፎች ቁጥር | 865,224 | 326,471,094 | 7,230 |
| ከቅድመ ዝግጅት በኋላ የቀሩ ልጥፎች | 527,522 | 906,471 | 7,230 |
| በሰውሰራሽ አስተምሮት ጥላቻ ንግግሮች ከተለዩ በኋላ የቀሩ ልጥፎች ቁጥር | 244,221 | 239,558 | 4,135 |
| ለትርጉም በዕጣ የተመረጡ ናሙናዎች | 2634 | 2107 | 2264 |

*ሰንጠረዥ 2: በእያንዳንዱ የመረጃ ዝግጅት ሂደት ላይ የነበሩት የልጥፎች ቁጥር፣ በመድረክ*

## የመረጃ ትርጓሜ

በጉዳዩ በቂ እውቀት ባላቸው ባለሙያዎችና በመረጃ ትርጓሜ ፕሮቶኮል መሠረት የተሰራው የመረጃ ትርጓሜ፣ ለመረጃ ዝግጅት ሂደቱ ቁልፍ ሚና ተጫውቷል። (ክፍል 1.2 አባሪ ላይ የትርጓሜ ፕሮቶኮሉ ተያይዟል)

የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ባለሙያዎች የያዘው ቡድን ተመሳሳይ የሆነ የትርጓሜ ዘዴ መጠቀሙንና ስለ ጥላቻ ንግግር ምንነት ያለው ሀሳብ ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነበር። የሲ.አይ.አር የሀሳብ ማዕቀፍ ለምደባ ፕሮቶኮሉ መሠረት ነበር። (ክፍል 3.1 ይመልከቱ) የመረጃ ትርጓሜው ላይ ለተሳተፉት ባለሙያዎች ስለ ጥላቻ ንግግር፣ ኢላማዎቹ፣ አይነቶቹና አውዶቹ በቂ የሆነ ትንተና ተሰጥቷል። (ለሙሉ የትርጓሜ ፕሮቶኮል ክፍል 7.2 አባሪ ይመልከቱ)። ፕሮቶኮሉ የጥላቻ ንግግር ኢላማዎችን፣ አይነቶችንና አውዶችን እንዴት በፅሁፍ ላይ መለየት እንደሚቻልና የትርጓሜ መሳሪያዎቹን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በምሳሌ የታገዘ ማብራሪያዎችን ሰጥቷል።

የመረጃ ትርጓሜ ባለሙያዎቹ መረጃዎቹን በጥላቻ ንግግር ኢላማ፣ አይነትና አውድ ለመከፋፈል ዶካኖ (Doccano) የተባለውን ታዋቂ መተግበሪያ ተጠቅሟል። ይህ ክፍፍልም በቀጣይ ያለውን ጥልቅ የሆነ የመረጃ ትንተና አሳልጧል።

ይህ አሰራር በጥናቱ ዙሪያ ያሉ ውስንነቶችንም አመላክቷል (ለውስንነቶቹ ክፍል 3.6 ተመልከቱ)። በመረጃ ትርጓሜ ባለሙያዎችና በመረጃ መሃንዲሶች መካከል የነበረው ውይይት በመረጃ ምደባው ወቅት ተመሳሳይ ህጎች እንዲተገበሩ አድርጓል (ክፍል 7.3 ይመልከቱ)።

### 3.5.1. የመረጃ ተረጓሚዎች

#### እንግሊዝኛ

ሁለት ባለሙያዎች በዕጣ የተመረጡ የእንግሊዝኛ ልጥፎችን እንዲተረጉሙ ተደርጓል። የትርጓሜ ፕሮቶኮሉን ያዘጋጀውና በኢትዮጵያ ዙሪያ ስላለው ሁኔታ በቂ እውቀት ያለው ባለሙያ ሁሉንም ልጥፎች ሲተረጉም ሁለተኛው

ባለሙያው ደግሞ የመጀመሪያው ባለሙያ ከተረጎማቸው አጠቃላይ ልጥፎች ውስጥ 10 ከመቶውን ተርጉሟል። ይህ አካሄድ በሁለት ተርጓሚዎች መካከል ያለውን ስምምነት ለመለካትና ስራው ወጥነት እንዲኖረው አግዟል።

**አማርኛ**

ሲ.አይ.አር ሶስት ባለሙያዎች በዕጣ የተመረጡ ልጥፎችን እንዲተረጉሙ አድረጓል። በማህበራዊ ሚዲያ ትንተና ላይ ልምድ ያላቸውና አማርኛ ተናጋሪ የሆኑ አንድ ባለሙያ ሁሉንም የአማርኛ መረጃ እንዲተረጉሙ ሲደረግ ሁለቱ ባላሙያዎች ደግሞ (የትግርኛና የአፋን አሮሞውን መረጃ የተረጎሙት ባለሙያዎች) የመጀመሪያው ባላሙያ ከተረጎሙት ውስጥ 10 ከመቶ የሚሆነውን መረጃ ተርጉመዋል። ከዚያም የጥናቱን ወጥነት ለማስጠበቅ በስራቸው መካከል ያለው ስምምነት ተለክቷል።

**ትግርኛ**

ሲ.አይ.አር የትግርኛ ልጥፎች በአንድ ሰው እንዲተረጎም አድርጓል። አኚህ ባለሙያ የአማርኛ ልጥፎችን እንዲተረጉሙ በማድረግ በባለሙያዎች መካከል ያለው ስምምነት በተለካበት ወቅት የጥላቻ ንግግሮችን ኢላማ፣ አይነትና አውድ የመለየት ብቃታቸውን ስላስመሰከሩ በድጋሚ በባለሙያዎች መካከል ያለውን ስምምነት መለካት አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም።

**አፋን ኦሮሞ**

ሲ.አይ.አር የአፋን ኦሮሞ ልጥፎች በአንድ ሰው እንዲተረጎም አድርጓል። አኚህ ባለሙያ የአማርኛ ልጥፎችን እንዲተረጉሙ በማድረግ በባለሙያዎች መካከል ያለው ስምምነት በተለካበት ወቅት የጥላቻ ንግግሮችን ኢላማ፣ አይነትና አውድ የመለየት ብቃታቸውን ስላስመሰከሩ በድጋሚ በባለሙያዎች መካከል ያለውን ስምምነት መለካት አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም።.

### 3.5.2. በተርጓሚዎች መካከል ያለ ስምምነት

በመመሪያዎች ተግበራዊነት ወቅት ወጥነት እንዲኖር በመረጃ ተርጓሚዎች መካከል ያለው ስምምነት በኮኸንስ ካፓ (Cohens koppa) እና ፌኢስ ካፓ (Feis kappa) መለኪያዎች ተፈትሸዋል። ውጤቱም በመረጃ ተርጓሚዎች መሃል ከበቂ እስከ መካከለኛ ስምምነት እንዳለ አሳይቷል (ለበለጠ መረጃ ክፍል 7.4 ይመልከቱ)።

## ውይይቶችና አውደ ጥናቶች

ሲ.አይ.አር እ.ኤ.አ በሐምሌና በታህሳስ 2023 አዲስ አበባ ውስጥ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ተከታታይነት ያላቸው ውይይቶችና አውደ ጥናቶች አካሂዷል። በሰብዓዊ መብት ዙሪያ የሚሰሩ ባለሙያዎችም የአነዚህ ውይይቶች ተሳታፊ ነበሩ። ሐምሌ ውስጥ የተካሄዱት ውይይቶች ለመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገሉና ጥላቻ ያዘሉ ቃላትን ለመምረጥ ጥሩ የመከራከሪያና ሀሳብን የማንሸራሸሪያ መድረክ ሆነው ነበር። ሲ.አይ.አር በእነዚህ ጊዜዎች ውስጥ 42 ሰዎችን አማክሯል። አብዛኞቹ በግል ተወክለው የመጡ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ 11 የተለያዩ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ድርጅቶችን ወክለው መጥተዋል። እነዚህ ውይይቶች 2058 ቁልፍ ቃላትን በ 4 ቋንቋዎች መለየት አስችለዋል።

እ.ኤ.አ በታህሳስ 2023 ሲ.አይ.አር የመጀመሪያ ዙር የጥናቱን ግኝቶች ለማቅረብ እና መፍትሄ ሀሳቦችን ለመቀበል በማሰብ ተከታታይ የሆኑ ውይይቶችንና አራት አውደ ጥናቶችን አካሂዶ ነበር። በድጋሚም ተጨማሪ ሰዎች በጥናቱ ላይ እንዲሳተፉ በማሰብ አራት የኢንተርኔት ላይ ውይይቶችን አካሂዷል። በአጠቃላይ ሲ.አይ.አር ከ18 ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ድርጅቶች የተወጣጡ 24 ሰዎችን አማክሯል። የእነዚህ አውደ ጥናቶች አላማ በሴቶች መብት፣ ፆታን መሠረት ባደረጉ ጥቃቶች እና በኢንተርኔት ደህንነት ዙሪያ ከሚሰሩ የተለያዩ ባለሙያዎች ጋር መወያየት ነበር። ሲ.አይ.አር በጉዳዩ ላይ በቂ እውቀት ያላቸውን ሰዎች በማናገርና ስለጥናቱና የችግሩ መፍትሄ ሀሳቦች ዙሪያ አስተያየቶችን ተቀብሏል። እያንዳንዶቹ ሁኔታዎች ስለሚለያዩና ለጥሩ ጥናት መሠረት ነው ብሎ በማሰብ ሲ.አይ.አር የብዙ ሰዎችን ድምፅ ጥናቱ ላይ አካቷል።

እ.ኤ.አ የካቲት 2024 ሲ.አይ.አር የጥናቱን ውጤቶች ተከታታይነት ባላቸው ስብሰባዎች ላይ በማቅረብና ግብረ መልሶችን ለሁለት ሳምንት በመቀበል የሁሉንም ድምፅ ለማካተት ሞክሯል።

## ውስንነቶች

ሲ.አይ.አር በተቻለ መጠን በጥናቱ ዘዴና ውጤቶቹ ዙሪያ ያሉ ውስንነቶችን ለመቀነስ ሞክሯል። ሆኖም ግን ከዚህ በታች የተገለፁ የተለያዩ የመረጃ፣ የአውድና የውጤት ውስንነቶች እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል።

### 3.7.1. ቋንቋዎች

ኢትዮጵያ ዉስጥ ከ80 በላይ ቋንቋዎች ይነገራሉ። ሁሉም ቋንቋዎች በኢንተርኔት ላይ ባይወከሉም በሃብትና ሰዉ ሃይል ዉስንነት ምክንያት በዚህ ጥናት ማካተት የተቻለዉ አራት ቋንቋዎች ብቻ ነዉ። በዚህም ምክንያት ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ በሰፊዉ የሚታዩ አራት ቋንቋዎች ተመርጠዋል፤ አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛና እንግሊዝኛ። በመሆኑም የዚህ ጥናት ግኝቶች በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የእያንዳንዱን አራት ቋንቋ ተናጋሪዎች ናሙና ብቻ ይወክላሉ። ይህም ሆኖ ጥናቱን በአራት ቋንቋ ማካሄድ በራሱ ከፍተኛ አቅምን የሚጠይቅ ነበር። አራቱን ቋንቋዎች የሚናገሩና ስለሀገሪቱ ሁኔታ የሚረዱ የጥናት ባለሙያዎችና የማህበራዊ ሚዲያ ተንታኞች አስፈልገዉም ነበር። ወደፊት ሲ.አይ.አር ለዚህ ጥናት የተጠቀመዉን ዘዴ በመጠቀም በሌሎች ቋንቋዎች ላይ ተመሳሳይ ጥናቶች መሰራት ይችላሉ።


### 3.7.2. መረጃ አሰባሰብ

ሲ.አይ.አር የእያንዳንዱን ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ህግና ደንብ ለማክበር በማሰብ ለእያንዳንዱ ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ የራሱ የሆነ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ተጠቅሟል። ይህ አስፈላጊ ቢሆንም ከተለያዩ መድረኮች ላይ የተለያዩ ቁጥር ያላቸዉ ልጥፎች እንዲገኙ ምክንያት ሆኗል። ለምሳሌ ሲ.አይ.አር ከኤክስና ቴሌግራም አንፃር ከፌስቡክ ላይ የሰበሰበው መረጃ አነስተኛ ነዉ። በዚህ ምክንያት ሲ.አይ.አር በእያንዳንዱ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ያለዉን የጥላቻ ንግግር መጠን ማወዳደር አልቻለም። ይልቁንም ከተወሰዱት መረጃዎች ውስጥ በፐርሰንት የጥቃቶቹ አይነትና አዉድ ማወዳደር ተችሏል።

መረጃ ለማሰባሰብ የፌስቡክ ገፆች በተመረጡበት ወቅት የጥናቱ ባለሙያዎች ጥናቱ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ አዝማሚያዎችን አስተዉለዋል። ለምሳሌ በፌስቡክ ላይ የሚቃጡ ጥቃቶች የታዋቂ ሰዎች ልጥፎች ላይ የሚሰጡ

አስተያየቶችን ጨምሮ አንድን ግለሰብ ኢላማ ያደረጉ ናቸዉ። የጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከፌስቡክ ግሩፖች በመሆኑ በግለሰቦች ላይ የሚቃጡ የጥላቻ ንግግር መረጃዎችን በጥናቱ ዉስጥ ማካተት አልተቻለም። በተወሰኑ ግለሰቦች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በተመለከተ ወደፊት የጥናት ሪፖርቶች ሊሰሩ ይችላሉ።

በፌስቡክ ግሩፖች ዉስጥ የሚገኙት ልጥፎች በላያቸዉ ላይ ፅሁፍ ያለባቸዉ ምስሎች እና ወሲባዊ ምስሎችን ያዘሉ እንደሆኑ የጥናት ባለሙያዎቹ ተመልክተዋል። በዚህ መልኩ የተሰነዘሩ የጥላቻ ንግግሮች በማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይለዩ ይችላሉ። ሲ.አይ.አር ወጣት ሴት ልጆች አዝነው ከሚያሳዩ ምስሎች ጎን "18 አመቴ ቢሆንም የወንድ ጓደኛ የለኝም" የሚል እና መሰል የተቀነባበሩ ፅሁፎች ያሉባቸው ልጥፎችን ተመልክቷል። ይህ ጥናት በፅሁፍ የተፃፉ ልጥፎች ላይ በማተኮሩ ምክንያት አንደዚ አይነት ሰዕላዊ ልጥፎች በዚህ ጥናት ዉስጥ አልተካተቱም። የወደፊት ጥናቶች ምስሎችና የተቀነባበሩ ስዕሎች ሴቶች ላይ በሚደርሰዉ የኢንተርኔት ጥቃት ላይ ያላቸዉን ተፅዕኖ ማጥናት ይችላሉ።




*ምስል 6: በዚህ ጥናት ውስጥ ሊካተቱ የማይችሉ ልጥፎችን የሚያሳይ ከፌስቡክ ላይ የተወሰደ ምሳሌ፣ የልጅቷ ፊትና (ታች በግራ በኩል) የገፆቹ ልዩ ስም እንዳይለዩ ተሸፍነዋል.*

Centre for Information Resilience

### 3.7.3 የመረጃ ዝግጅትና አመራረጥ

ሲ.አይ.አር መረጃዎችን ለጥናቱ ከመምረጡ በፊት የአርተፊሻል አስተምሮት ሞዴልን (Pre-trained machine learning model) ተጠቅሞ ጥላቻ ያልሆኑ ልጥፎችን በማስወገድ ጥላቻ አዘል የሆኑት ልጥፎች በቀላሉ እንዲገኙ አድርጓል። ሆኖም ይህ ሞዴል በትግርኛና በአፋን ኦሮሞ ቋንቋዎች የሰለጠነ ስላልሆነ ይህን የቅድመ ዝግጅት ሂደት በእነኚህ ቋንቋዎች ላይ መተግበር አልተቻለም። ይህን ሞዴል ማስተማሪያ የሆኑ መረጃዎች በትግርኛና አፋን ኦሮሞ አለመኖራቸዉ የዚህ ክፍተት መንስኤ ነዉ። ስለዚህም ሲ.አይ.አር ያዘጋጃቸዉ የመረጃ ትርጉሞች ወደፊት በእነዚህ ቋንቋዎች ሞዴሎችን ለማዘጋጀት ጠቃሚ ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ ሞዴሎች የጥላቻ ንግግሮችን በራሳቸዉ መለየት ስለሚችሉ ለተለያዩ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ይዘት ተቆጣጣሪዎችም ጠቃሚ ይሆናል ።

ሲ.አይ.አር የሰበሰበዉ የመረጃ መጠን በሙብዛቱ ምክንያት ናሙናዎች በዕጣ መመረጣቸው ብዙ የትንተና ዉስንነቶችን ፈጥሯል። ሲ.አይ.አር ከኤክስ ላይ 865,224 ልጥፎችን፣ ከቴሌግራም ላይ 326,471,094 ልጥፎችን እንዲሁም ከፌስቡክ ላይ 7230 ልጥፎችን ሰብስቧል። ይህም የቅድመ ዝግጅት ስራዉን ማዳተት ጨምሮ የተለያዩ ተግዳሮቶችን ፈጥሯል። የቅድመ ዝግጅት ሂደቶች ከታለፉም በኋላ የቀረዉ የመረጃ መጠን ካለው ውስን የሰዉ ሃይል አንፃር ስለበዛ ሲ.አይ.አር ከእያንዳንዱ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ዕጣ ልጥፎችን መርጧል። ይህ በመሆኑ በጊዜ ሂደት ዉስጥ ያለዉን የጥላቻ ንግግር ብዛት ለዉጥ ወይም የጥላቻ ንግግሮች የሚጨምሩባቸዉ ወቅቶችን (ከኢንተርኔት ዉጪ ባሉ ክስተቶች) መመርመር አልተቻለም። በተጨማሪም ይህ አይነቱ የመረጃ አመራረጥ የጥላቻ ንግግር በሚያሰራጩ የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች መካከል ያለዉን ግንኙነት ጥናቱ እንዳያይ ምክንያት ሆኗል። ሲ.አይ.አር የመጀመሪያዉን መረጃ ስብስብ ስለስቀመጠ የወደፊት ጥናቶች የተወሰኑ የማህበራዊ ሚዲያ ገጾች ለአብዛኛዉ የጥላቻ ንግግሮች መንስኤ ይሆኑ እነደሆን መመርመር ይችላሉ።

### 3.7.4. ተደረራቢ ጥቃቶች

ሲ.አይ.አር ይህን ጥናት በማስፋት የተለያዩ ማንነቶችን በአንድ ጊዜ የሚያጠቁ የጥላቻ ንግግሮችን ለማየት ሞክሯል። በመጀመሪያ የጥናቱ ትኩረት በፆታ ላይ ያነጣጠሩ ጥላቻ ንግግሮች ላይ ብቻ ነበር። ሆኖም ይህ ከሌሎች ማንነቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጥናት ሌሎች የጥላቻ ኢላማ በሆኑ የማንነት መገለጫዎች ዙሪያ መረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም ምክንያት የቁልፍ ቃላቶቹ ስብስብ ከሌሎች ህጋዊ ከለላ ካገኙ ማንነቶች (ለምሳሌ ብሔርና ሃይማት) ጋር የተገናኙ ቃላቶችንም ያካተተ ነበር። ሲ.አይ.አር ይህንን የቃላት ስብስብ በመጠቀም በፆታ ላይ ብቻ ሳይሆን በብሔር፣ በሀይማኖት፣ በዘርና በአካል ጉዳተኝነት ላይ በሚፈፀሙ የጥላቻ ንግግሮች ዙሪያ የመረጃ ቋት አዘጋጅቷል። ወደፊት የሚሰሩ ጥናቶች እነዚህን መረጃዎች በመጠቀም በሌሎች ማንነቶች ላይ ስለሚደርሱ የጥላቻ ንግግሮች ጥናት መስራት ይችላሉ።

### 3.7.5. የመረጃ ትርጓሜ

ሲ.አይ.አር የተወሰነ መረጃ መርጦ በተርጓሚዎች መካከል ያለውን ስምምነት ማረጋገጥ አስፈላጊ እንደሆነ አምኗል። ይህ ሂደት የመረጃ ትርጓሜ ሂደቱን ቢያዳትተውም በመረጃ ተርጓሚዎቹ ግንዛቤና በስራው ወጥነት ዙሪያ በራስ መተማመን እንዲኖር አድረጓል።

የትርጓሜ ፕሮቶኮሉ በሚዘጋጅበት ወቅት አንድን ይዘት ጥላቻ ነው ወይም አይደለም ብሎ ለመመደብ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ታይቷል። አንዳንድ ልጥፎችን ለመመደብ አስቸጋሪ ስለነበረ  የመረጃ ተርጓሚዎች አርስ በአርስ ሲመካከሩም ነበር። የትርጓሜውን ፕሮቶኮል በጥብቅ ለመተግበር በሚደረገው ጥረት አንዳንድ ልጥፎች የጥላቻ ንግግር ያዘሉ ሊሆኑ ቢችሉም በፕሮቶኮሉ መሠረት መስፈርቱን ስላላሟሉ መወገዳቸው የሲ.አይ.አርን የመረጃ መጠን ገድቦታል። ለምሳሌ አንዳንድ የጥላቻ ልጥፎች የጥቃት ኢላማ ስለሌላቸው ተወግደዋል።

በተጨማሪም የመረጃ ትርጓሜው ፅሁፍን መሠረት ያደረገ እንጂ አውድን ወይም ምስልን ያካተተ ካለመሆኑም በተጨማሪ በመረጃ ተርጓሚዎች መካከል ፅሁፎችን በደፈናው ለመውሰድ ስምምነት ተደርሶ ነበር። ለምሳሌ የመረጃ ተርጓሚዎቹ 'ኒጋ' እና 'ኒገር' የተባሉ ጥቁሮችን ዝቅ የሚያደርጉ ቃላቶች ፆታን መሠረት ካደረጉ ጥላቻ ንግግሮች ጋር በተጓዳኝ እንደሚታዩ አስተውለዋል። እንዲያውም አንድ የአውደ ጥናት ተሳታፊ እነዚህ ቃላቶች በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ጥላቻ ሳይሆን እንደ ሙገሳ እንደሚታዩ ገልጸዋል። በዚህም ምክንያት የትርጓሜ ፕሮቶኮሉን በጥብቅ ለመተግበር ሲባልና ልጥፎችን በደፈናው ለመውሰድ በተደረሰው ስምምት ምክንያት አንደዚህ አይነት ልጥፎች በተሳሳተ መንገድ እንደ ጥላቻ ንግግር ተመድበው ይሆናል። በተቃራኒው ልጥፎች በደፈናው መወሰዳቸው የጥናቱን መረጃ መጥን ሊያሳንሰው ይችላል።ለምሳሰሌ 'እሷ' ወይም 'አንቺ' የሚሉት ቃላቶች ለወንድ ልጅ እንደ ስድብ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። የቃላት ትርጓሚዎች አውድን ባለማከተታቸውና ቃላቶቹ ብቻቸውን ጥላቻን ስለማያንፀባርቁ ጥናቱ ውስጥ ሳይካተቱ ቀርተዉ ይሆናል። በዚህም ምክንያት ሲ.አይ.አር የዚህ ጥናት ዉጤቶች የችግሩን ጫፍ ብቻ እንደሚያሳዩ ያምናል። በመረጃ ትርጓሜ ዙሪያ ስለነበሩት ፈተናዎች በጥልቀት ለመመልከት ወደ ክፍል 7.2 ይሂዱ

# 4. ዉጤቶችና ዉይይቶች

ይህ ጥናት በ3 ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች (ኤክስ፣ ቴሌግራምና ፌስቡክ) ላይ ያሉ፣ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ያነጣጠሩ የጥላቻ ንግግር አይነቶችን በመመርመር ኢትዮጵያ ዉስጥ ላለዉ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ጠንካራ ማስረጃ ለማቅረብ ያለመ ነዉ። ሲ.አይ.አር የጥቃቶቹን ተፈጥሮ ለመረዳት በማሰብ የጥቃቶቹን አውድ አጥንቷል። ለምሳሌ ጥቃቶቹ አፀያፊ፣ በስርዐተ-ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ፣ ጠብ ጫሪ ወይስ ፌዝ የያዙ መሆናቸውን ለይቷል። በተጨማሪም ሲ.አይ.አር በማህራዊ ሚዲያ መደረኮች ላይ ያሉትን የፆታ ልዩነቶች አጥንቷል። የጥቃቶቹ አይነት፣ አውድና ኢላማ የያዘ ማብራሪያ በክፍል 3.1 እና በመረጃ ትርጓሜ ፕሮቶኮል ክፍል 7.2 ላይ ይገኛል።

ሲ.አይ.አር ሴቶችና ልጃገረዶች ከፆታቸው በተጨማሪ በሌሎች ህጋዊ ከለላ ባገኙ ማንነቶቻቸው (ብሔርና ሀይማት) ሲጠቁ ያለውን ልዩነት ለማጥናት በሌሎች ማንነትቶች ላይ የሚደርሱ ጥላቻ ንግግሮችን አጥንቷል። ሌሎች የጥቃት ኢላማ በሆኑ ማንነቶች ዙሪያ መረጃዎችን በመሰበሰብ ፆታን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮችና ሌሎች ማንነቶችን (ብሔር፣ ሀይማኖትና ዘር) ኢላማ ባደረጉ የጥላቻ ንግግሮች መካከል ያለውን የይዘት ልዩነት ለማጥናት ተችሏል። በቃለ መጠይቆች (የሲ.አይ.አር የመጀመሪያው ጥናት ላይ የተደረጉት)፣ ውይይቶችና አውደ ጥናቶች ላይ የተነሱ ሀሳቦች እንደየአስፈላጊነታቸው በዚህ ጥናት ውስጥ ተካተዋል።

## 4.1 ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ ፆታዊ የጥላቻ ንግግሮች

ሲ.አይ.አር ከዚህኛው በፊት ባከናወነው ጥናት፣ በውይይቶች፣ በአውደ ጥናቶችና በእዚህ ጥናት ላይ የተገኙ ውጤቶች እንደሚያሳዩት ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሴቶችና ልጃገረዶች የተለያዩ አይነት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ይደርስባቸዋል። ይህም የጥላቻ ንግግር፣ ወሲባዊ ምስሎችን ያለፍቃዳቸው መልቀቅ እና ትንኮሳን ያካትታል። ይህ ጥናት አድማሱን በማጥበብ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ካደረጉ ጥቃት አይነቶች ውስጥ የጥላቻ ንግግርን አይነት፣ አውድና ኢላማ ይመለከታል።

በጥናቱ መሰረት "ስድቦች" ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ካነጣጠሩ የጥላቻ ንግግር "አይነቶች" የመጀመሪያውን ደረጃ ሲይዙ "አፀያፊ" ንግግሮች ደግሞ ከጥላቻ ንግግር "አውዶች" ውስጥ በሰፊው የሚታዩት ናቸው። ውሳኔ ሰጪ አካላት ይህን መረጃ በመጠቀም ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግሮች ላይ ያነጣጠሩ መፍትሔዎችን መስጠት ይችላሉ፤ ለምሳሌ ሴቶችን አሳንሰው የሚያዩ አስተሳሰቦችን ለማስቀረት ያለሙ ዘመቻዎችን በማጠናክር።

### 4.1.1. ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አይነቶች


ሲ.አይ.አር በተሰበሰበው መረጃ ውስጥ ያሉትን የጥላቻ ንግግር 'አይነቶች' መርምሯል (ስድብ፣ ዛቻ፣ ፆታን ከባህሪዎች ጋር የሚያገናኙ እና አሳንሰው የሚያዩ)።

| TYPE OF HATE SPEECH | | | | |
|---|---|---|---|---|
| CATEGORY | INSULT | THREAT | PRESUMED ASSOCIATION | ALLEGED INFERIORITY |
| DEFINITION | Insults or denigrating expressions | Intimidation, incitement to hatred, violence, violation of rights | with personality traits, e.g. laziness, greed | e.g. of social position, cognitive or physical ability |

*ምስል 7: በጥናቱ ዘዴ ላይ በተገለዐው መሰረት የእያንዳነዱ ምድብ ተርጓሜ*

‘ስድቦች’ ከአጠቃላይ ጥቃቶች 36.6 ከመቶ በመያዝ ዋናውን ድርሻ ይይዛሉ። ሴቶችና ልጃገረዶችን ስንፍናና ስግብግብነትን ጨምሮ ከሌሎች መጥፎ ባህሪዎች ጋር የሚያገናኙ (ሙሉ ዝርዝሩን ክፍል 7.2 በሚገኘው ትርጓሜ ፕሮቶኮል ላይ ይመልከቱ) የጥላቻ ንግግሮች በ27.7 ከመቶ ሁለተኛውን ደረጃ ይይዛሉ

“አሳንሰው የሚያዩ/የበታችነት“ ንግግሮች ወይም ሴቶችንና ልጃገረዶችን በማህበራዊ ሚናቸው፣ በአስተሳሰባቸው ወይም በአካላዊ ብቃታቸው አሳንሰው የሚያዩ የጥላቻ ንግግሮች ከአጠቃላይ የጥላቻ ንግግር አይነቶች ውስጥ 22.2 ከመቶውን በመያዝ ቀጣዩን ደረጃ ይይዛሉ። ማስፈራሪያዎች፣ ዛቻዎች ወይም ጥላቻና ጠብ ቀስቃሽ የሆኑ የጥላቻ ንግግሮችን የያዘው የ”ዛቻ“ የጥላቻ ንግግር አይነት 13.4 ከመቶ ይይዛል ።




*ምስል 8: ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አይነቶች ስብጥርን የሚያሳይ ምስል*

### 4.1.2. ሴቶችን ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አውዶች

ሲ.አይ.አር ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮችን 'አውድ' ለመረዳት የጥላቻ ንግግሮቹ 'ጠብ ጫሪ'፣ 'አፀያፊ'፣ 'በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሰሳቱ አመለካከቶችን' የሚያንፀባርቁ ወይም 'የፌዝ' ቋንቋዎችን መያዛቸውን ተመልክቷል፡፡[18]

| SENTIMENT OF HATE SPEECH | | | | |
|---|---|---|---|---|
| CATEGORY | OFFENSIVE | STEREOTYPICAL | MOCKERY | AGGRESSIVE |
| DEFINITION | Insulting, demeaning or denigrating language. Associating the target with harmful or false personal traits, or suggesting the target's inferiority. | Text includes implicit or explicit references to stereotypical beliefs or prejudices about an individual/group with protected characteristics. | Mockery, satire or sarcastic messaging which targets a protected characteristic of the recipient and could be harmful. | Strong language that physically intimidates, threatens or incites physical violence against the recipient, or which requests, suggests or promotes a violation of the recipients' rights. |


*ምስል 9: በጥናቱ ዘዴ ላይ በተገለፀው መሰረት የእያንዳንዱ ምድብ ተርጓሜ*

'አፀያፊ' ቋንቋዎች 42.6 ከመቶ ድርሻን በመያዝ ከሁሉም የጥላቻ ንግግር አውዶች የመጀመሪያ ደረጃን ይይዛሉ፡፡ ይህም ተሳዳቢና አዋራጅ ከሆኑ ቋንቋዎች ጀምሮ ኢላማውን ከመጥፎ ባህሪያት ጋር በማገናኘት የኢላማውን የበታችነት የሚያሳዩ ቋንቋዎችን ያካትታል፡፡

የጥቃቶቹን አውድ ስንመለከት በሁለተኛነት 'በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሰሳቱ አመለካከቶችን' የያዙ የጥላቻ ንግግሮች በ26.2 ከመቶ ይከተላሉ፡፡ እነዚህ ልጥፎች በግለሰቦች ወይም በቡድኖች ላይ በፆታቸው ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጭፍን ጥላቻን የሚያራምዱ ናቸው፡፡ 'የአሽሙር' ቋንቋዎች በ20.3 ከመቶ ተከታዩን ደረጃ ይይዛሉ እነዚህ ልጥፎች አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ ፆታን ኢላማ በማድረግ የሚሰነዘሩ ቀልዶች፣ ስላቆች ወይም የሽሙጥ ንግግሮች ናቸው፡፡

በመጨረሻም ከሌሎች ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ካደረጉ የጥላቻ ንግግር አውዶች አንፃር 'ጠብ ጫሪ' ንግግሮች በ7.3 ከመቶ ዝቅተኛውን ደረጃ ይይዛሉ፡፡ 'ጠብ ጫሪ' ንግግሮች ማስፈራሪያዎችን፣ ዛቻዎችን፣ ኢላማው ላይ አካላዊ ጥቃት እንዲያደርሱ የሚያበረታቱ ንግግሮችን ወይም የሰብዓዊ መብት ጥሰትን የሚቀሰቅሱ ልጥፎችን ያካትታል ፡፡

[18] Full definitions of each of these categories can be found in section 3.1 and the annotation protocol in section 7.2




*ምስል 10፡ ሴቶችን ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አውዶች ስብጥርን የሚያሳይ ምስል.*

### 4.1.3. ማብራሪያ፡ ሴቶችንና ልጃገዶችን ኢላማ ያደረጉ  የጥላቻ ንግግሮች

'ስድቦች' እና 'አፀያፊ' ንግግሮች ከሁሉም የጥላቻ ንግግር ይዘቶች በአብዛኛው ተንጸባርቀዋል፡፡ የጥናቱ የመጀመሪያ ግኝቶች በህዳር እና ታህሳስ 2023 በተካሄዱት ስምንት የተለያዩ አውድ ጥናቶች ላይ በቀረቡበት ወቅት 'ዛቻዎች' እና 'ጠብ ጫሪ' ንግግሮች ዝቅተኛ ደረጃ መያዛቸው ተሳታፊዎቹን አስገርሞ ነበር፡፡ 'ዛቻዎች' እና 'ጠብ ጫሪ' ንግግሮች ሲ.አይ.አር. ካቀረበው ቁጥር በላይ እንደሆኑም ገልፀዋል፡፡ ውይይቶቹ ሲቀጥሉም ዛቻ አዘልና ጠብ ጫሪ የሆኑ ንግግሮች ሊጠቆሙና ከማህበራዊ ሚዲያ ትስስር ድህረ-ገፅ ላይ ሊወገዱ ስለሚችሉ ቁጥሮች ሊያንሱ እንደሚችሉ ሌሎች ተሳታፊዎች አንስተዋል ፡፡ በተጨማሪም በመረጃ ትርጓሜ ወቅት አውዳዊ መረጃ አለመካተቱና የትርጓሜ ፕሮቶኮሎች በጥብቅ መተግበራቸው ሁሉም ዛቻና ጠብ ጫሪ ንግግሮች እንደ ጥላቻ ንግግር እንዳይመደቡ አድርጎ ሊሆን ይችላል፤ ለምሳሌ የጥቃቱ ኢላማ በግልፅ ካልታወቀ መረጃው ሊወገድ ይችላል፡፡

አብዛኞቹ ባለ ድርሻ አካላት በውጤቶቹ ቢገረሙም ምላሻቸው፣ ሲ.አይ.አር 'ብዙም ያልከፉ' በሚባሉ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች መለመድና ትኩረት ማጣት ዙሪያ ከሲቪል ማህበራትና ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ጋር ካደረገው ውይይት ጋር የሚስማሙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ብዙዎቹ የአውደ ጥናት ተሳታፊዎች ስድቦች፣ ፆታን ከመጥፎ ባህሪ ጋር የሚያያይዙ ወይም አሳንሰው የሚያዩ የጥላቻ ንግግሮች ትኩረት እንደማይሰጣቸው ገልፀዋል። አንድ ተሳታፊ አንደዚህ አይነት የጥላቻ ንግግሮች ጉዳት አያመጡም ተብሎ ስለሚታሰብ ሪፖርት እንደማይደረጉና ትኩረት እንደማይሰጣቸው ገልፃለች፡፡ ብዙ ተሳታፊዎች በሰብዓዊ መብት ሴክተር ውስጥ ቢሰሩም 'ስድቦችን'፣ 'ፆታን ከመጥፎ ባህሪ ጋር የሚያገናኙ' ንግግሮችን ወይም "አሳንሰው የሚያዩ" ንግግሮችን እንደ ጥላቻ ንግግር እንደማይመድቧቸውና በጉዳቱ ላይ ያተኮሩና ጥልቅ የሆኑ የዕውቀት ማስጨበጫ ዘመቻዎች እንደሚያስፈልጉ ገልፀዋል ፡፡

በአውደ ጥናቶች ወቅት ሲ.አይ.አር የኢንተርኔት ላይ ጥቃት ሰለባ የነበሩትን ሰዎች በማናገር በሰራው የመጀመሪያው ጥናት ላይ የነበረ አንድ ቁልፍ ነጥብ ተነስቷል ፣ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ያለው ፆታን መሰረት ያደረገ የጥላቻ ንግግር በጣም ከመስፋፋቱ የተነሳ የተለመደና ትኩረት የማይሰጠው እንደሆነ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች አንስተው ነበር ። የጥላቻ ንግግር መለመድና በጥላቻ ንግግር ምንነት ዙሪያ ያለው የእውቀት ማነስ 'ጠብ ጫሪ' እና 'ዛቻ' ያልሆኑ የጥላቻ ንግግሮች ሪፖርት እንዳይደረጉ ምክንያቶች እንደሆኑ የአውድ ጥናቱ ተሳታፊዎች ተስማምተዋል። እነዚህ ግኝቶች በመጀመሪያ እይታ ጎጂ በማይመስሉ የጥላቻ ንግግሮች ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንደሚያስፈልግ ያጠናክራሉ።

ይህ ግኝት በሴቶችና ልጃገረዶች ሚናና መብት ዙሪያ ሰፋ ያለ ትምህርት እንደሚያስፈልግ ያሳያል። ለምሳሌ ሴቶችና ልጃገረዶች ባላቸው ሚና ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ የጥላቻ ንግግሮች በሰፊው እንደሚደርስባቸው ገልፀዋል። በተመሳሳይ የሲ.አይ.አር የመጀመሪያ ጥናት ላይ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው የጥቃት ሰለባዎች ከመልካቸውና ማህበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ሚና አንፃር ዝቅ የሚያደርጉ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ሲደርስባቸው ወንዶች ግን ባላቸው ፖለቲካዊ አመለካከት ጥቃት እንደሚደርስባቸው ገልፀዋል። በትምህርት ቤቶች፣ ስራ ቦታዎች እና በሀይማኖታዊና ፖለቲካዊ ተቋማት ውስጥ ስለ ፆታዊ ሚናና ፆታን መሰረት ስላደረጉ ጥቃቶች የተሻለ ትምህርት መስጠት ከፆታ ሚና ጋር የተያያዙ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ለመቅረፍ ይጠቅማል። ይህም ሴቶችና ልጃገረዶች በኢንተርኔት ላይም ሆነ ከኢንተርኔት ውጪ የተሟላና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያግዛል።

## 4.2 ሴቶችንና ልጃገረዶችን ብቻ ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች በመድረክ

በዚህ ጥናት ላይ የተካተቱ ሶስቱም የማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥላቻ ንግግሮችን የሚከለክል ፖሊሲ አላቸው። ሆኖም ግን እያንዳንዱ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ይዘቶችን የሚቆጣጠርበት መንገድና የተቆጣጣሪዎቹ ብዛት ስለሚለያይ ችግሩን የሚከላከሉበት መንገድ እንደ አጠቃላይ የተለያየ ነው። እያንዳንዱ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ የተለያዩ ዓይነት ተጠቃሚዎችም አላቸው። በዲጂታል ኢትዮጵያ ሪፖርት መሰረት እ.ኤ.አ በ 2023 ከማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ውስጥ ሴቶችና ልጃገረዶች 43.1 ከመቶዎን ብቻ ይሸፍናሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ተጠቃሚ በፆታ ተሰልቶ ባይቀመጥም የማስታወቂያ ምልከታ ቁጥሮችን በመመልከት ተቀራራቢ ቁጥር ማግኘት ይቻላል። ይህን መረጃ ተጠቅመን ስናይ ሴቶች ከፌስቡክ ተጠቃሚ ውስጥ 34.2 ከመቶ ሲይዙ ከኤክስ ተጠቃሚዎች ደግሞ 16.7 ከመቶውን ይይዛሉ። በቴሌግራም ላይ ተመሳሳይ መረጃዎች አልተገኘም ።

ሲ.አይ.አር በሰራው የመጀመሪያ ጥናት ተሳታፊዎች የተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮችን ለተለያየ አላማ እንደሚጠቀሙ ተናግረዋል። ከዓላማዎቹም መካከል መረጃ ለማግኘት፣ ሀሳባቸውን ለማጋራት፣ ስራቸውን ለማስተዋወቅ፣ ድምፃቸውን ለማሰማት ወይም ዘመድና ጓደኞቻቸውን ማግኘት ያካተተ ነበር። ሴቶችና ልጃገረዶች የትኛውን ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ እንደሚጠቀሙና ለምን እንደሚጠቀሙ መረዳት በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል ተስማሚ መፍትሄ ሀሳቦችን ይሰጣል ።

ይህ ጥናት ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር "አይነቶች" በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች መካከል ልዩነት እንዳላቸው ተረድቷል። በንፅፅር ብዙ 'ስድቦች' ከሌሎች ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ይልቅ ኤክስ ላይ ታይተዋል። ቴሌግራም ብዙ 'ዛቻዎች' ሲኖሩት ፌስቡክ ደግሞ 'ፆታን ከመጥፎ ባህሪያት ጋር የሚያያይዙ' እና


'አሳንሰው የሚያዩ' የጥላቻ ንግግሮች በሰፊው ይታዩበታል። በሶስቱም ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ 'አፀያፊ' የጥላቻ ንግግሮች ከሌሎች የጥላቻ 'አውዶች' በልጠው ታይተዋል።

### 4.2.1. ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አይነቶች በመድረክ

ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አይነቶች በሶስቱ ማህበራዊ ሚዲያዎች መድረኮች ላይ የተለያዩ ነበሩ። ኤክስ ላይ ከነበሩ ንግግሮች 48 ከመቶ (ኤክስ ላይ ጥላቻ ንግግር ተብለው ከተለዩት) 'ስድቦች' ሲሆኑ 'ስድቦች' በቴሌግራም ላይ 32.5 ከመቶ ፌስቡክ ላይ ደግሞ 25 ከመቶውን ይይዛሉ።

በንፅፅር ፌስቡክ በውስጡ "ፆታን ከባህሪ ጋር የሚያያይዙ" የጥላቻ ንግግሮችን (ለምሳሌ ሴትነትን ከስግብግብነት ጋር) በብዛት (31.7 ከመቶ) ይይዛል። በኤክስ ላይ እነዚህ የጥላቻ ንግግር አይነቶች 25.3 ከመቶ ይይዛሉ ። በተመሳሳይ ፌስቡክ በንፅፅር ሴቶችን "አሳናሽ/የበታች ያደረጉ" የጥላቻ ንግግሮች በብዛት ( 29.8 ከመቶ ) ይይዛል። እነዚህ አይነት ንግግሮች በቴሌግራም 23.7 ከመቶውን በኤክስ ደግሞ 16.7 ከመቶውን ይይዛሉ።

በመጨረሻም ከፌስቡክ (13.5 ከመቶ ) እና ኤክስ (10 ከመቶ) ጋር ሲወዳደር ቴሌግራም ላይ 'ዛቻዎች' ይበዛሉ (15.6 ከመቶ)። ይህም ከፊስቡክና ኤክስ ጋር ሲወዳደር ቴሌግራም ዝግ መድረክ መሆኑና ይዘቶችን ተቆጣጥሮ ማስወገድ ስለሚያስቸግር ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሰባል።





*ምስል 11: ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አይነቶች በኤክስ፣ ቴሌግራምና ፈአስቡክ ላይ ያላቸው ስብጥርን የሚያሳይ ምስል*

### 4.2.2. ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አውዶች በመድረክ

ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አውዶች በሶስቱ ማህበራዊ መድረኮች ላይ የተለያዩ ነበሩ። በሶስቱ ማህበራዊ ሚዲያዎች እንደ አጠቃላይ ሲታይ 'አፀያፊ' ንግግሮች ከሌሎች የጥላቻ ንግግር 'አውዶች' አንፃር በሰፊው ታይተዋል።

ኤክስ ‘በስርዓተ-ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን’ የሚያንፀባርቁ የጥላቻ ንግግሮች በስፋት (የጥላቻ ንግግር ተብለው ከተለዩ ልጥፎች ውስጥ 31.6 ከመቶ) የሚታይበት ሲሆን እንደዚህ አይነት ንግግሮች በቴሌግራም ላይ 28.6 ከመቶ እንዲሁም በ ፌስቡክ ላይ 12.5 ከመቶውን ይይዛሉ። ከፌስቡክ (19.3 ከመቶ) እና ኤክስ (9.3 ከመቶ) ጋር ሲወዳደር ቴሌግራም የበለጠ (29.1 ከመቶ) ‘የፌዝ’ ይዘት ያላቸው የጥላቻ ንግግሮች ይታዩበታል። ፌስቡክ ከኤክስ (6.7 ከመቶ) እና ቴሌግራም (5.9 ከመቶ) ጋር ሲወዳደር ‘ጠብ ጫሪ’ የሆኑ ንግግሮች በብዛት (12.5 ከመቶ) ይታዩበታል።




*ምስል 12: ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግር አውዶች በኤክስ፣ ቴሌግራምና ፈአስቡክ ላይ ያላቸው ስብጥርን የሚያሳይ ምስል*

### 4.2.3. ማብራሪያ፡ ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች በመድረክ

ሲ.አይ.አር ከዚህ በፊት ባካሔደው ጥናት ላይ ተሳታፊ የነበሩ የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በሚጠቀሟቸው ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ በሰፊው እንዳለ ገልፀዋል። እንደ ሲ.አይ.አር የማህበራዊ ሚዲያ ትንተና ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥላቻ ንግግሮች በሶስቱም ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ በሰፊው ቢታዩም የጥቃቶቹ አይነትና አውድ ግን የተለያዩ ነበሩ። ልዩነቶቹን መረዳት ለችግሮቹ ተስማሚ የሆኑ መፍትሔዎችን ለመስጠት ከማገዙም በተጨማሪ ሴቶች ራሳቸውን እንዲከላከሉ የተሸሉ አማራጮችን ይፈጥራሉ። አንድ የመፍትሔ መንገድ ለሁሉም ማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ወይም ተጠቃሚ ላይሰራ ይችላል ።

በሁለተኛው ጥናት አውደ ጥናቶች ተሳታፊዎች መሰረት ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ያሉ ይዘቶች ጎጂ ቢሆኑም ሆነ ቢጠቆሙም አይወገዱም። ፌስቡክ ከኤክስ ይልቅ የተጠቆሙ ሪፖርት የተደርጉ ይዘቶችን በማውረድ የተሻለ ነበረ። እንደ አንድ ተሳታፊ ገለፃ ኤክስ ላይ ዛቻዎች ደርሰውባት ብዙ ሰዎች ይዘቱን ቢጠቁሙትም ከወራት በኃላ መድረኩ ላይ ይዘቱ እንደነበረ ገልፃለች። ሌሎች ተሳታፊዎች ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ  የሲቪል ማህበራት የፌስቡክን የቁጥጥር ስራ ለማገዝ አነጋጋሪ በሆኑ ጊዚያዊ ጉዳዮች ዙሪያ ለፌስቡክ መረጃ እንደሚልኩ ገልፀዋል። ይህ ጥሩ እርምጃ ሆኖ ሳለ ብዛት ያላቸውን የጥላቻ ንግግሮች ለመከላከል በተለያዩ ቋንቋዎች ተጨማሪ ጥረቶች ያስፈልጋሉ።

ሌሎች የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ጎጂ የሆኑ ይዘቶች በማስወገድ ዙሪያ ንቁ ናቸው። ቴሌግራም በዚህ ጥናት ከተካተቱ የቴሌግራም ግሩፖች ውስጥና በዚህ ጥናት ላይ እንደ ቁልፍ ቃላት ተብለው ከተመረጡት ቃላት ውስጥ በትንሹ ሁለት ቃላትን የያዙ 94,640.435 ልጥፎችን ማስወገዱ ሲ.አይ.አር ተመልክቷል።

ሲ.አይ.አር ያልተወገዱትን ልጥፎች ካጠና በኃላ ቴሌግራም ከሌሎች ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች አንፃር የፌዝ ንግግሮች እንደሚበዙበት ተረድቷል። በአውደ ጥናቶቹ ላይ እንደሚታየው ብዙ ተሳታፊዎች ፌዝን እንደ ጥላቻ ንግግር አያዩትም። ይህም ግኝቶች የስላቅ ይዘት ያላቸው የጥላቻ ንግግሮች የመጠቆምና የመወገድ እድላቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያሉ። በሌላ በኩል ጥቃት አድራሾቹ ስላቅን ወይም አሽሙርን ልጥፎታቸው እንዳይወገድባቸው እንደ አንድ ዘዴ እየተጠቀሙበት ሊሆን ይችላል። የቴሌግራም ተጠቃሚዎች ላይ ያተኮረና አሽሙር ወይም ስላቅ የጥላቻ ንግግር እንደሆነ የሚገልፅ ትምህርት መስጠት በጉዳዩ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ያግዛል። ለምሳሌ የቴሌግራም ተጠቃሚዎችን ስላቅ የያዙ የጥላቻ ንግግሮችን ስለመጠቆም ወይም የስላቅ ንግግሮችን የሚቃወሙ ይዘቶችን እንዲሰሩ ማሰልጠን ይቻላል። እንደዚህ አይነት ችግሮች ላይ ትኩረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎች ሰፊ የሆኑ የፖሊሲ መፍትሔዎችን ያግዛሉ ።

ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥላቻ ንግግሮች አወድ ዙሪያ አስተማማኝ መረጃ መኖሩ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ያላቸዉን ግንዛቤ በማሻሻል በይዘት፣ በቁጥጥርና በማስወገድ ዙሪያ ያላቸዉን ፖሊሲ እንዲያሻሽሉ ያግዛል። በተጨማሪም በማህበራዊ መድረካቸዉ ላይ ያለዉን የጥላቻ ንግግር አይነት በመረዳት የማህበረሰባዊ መመሪያቸዉን ሊያጠናክሩ ይችላሉ። ስለ ጥላቻ ንግግር ምንነት፣ስለጎጂ ተፅዕኖዎቹ እና ጥላቻ ንግግሮችን እንዴት ለማህበራዊ ሚዲያ መድረኩ ጥቆማ እንደሚሰጥ ማህበረሰቡን ማሳወቅ፣ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮቹ ለሚያደርጉት የቁጥጥር ስራዎች ተጨማሪ እገዛ ይሆናል። ወደፊት የሚሰሩ ጥናቶች ይህን ጥናት በማስፋት እንደ ቲክቶክ እና ዩቲዩብ ባሉ ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ማተኮር ይችላሉ።

## 4.3 ፆታዊ ንፅፅር


የዚህ ጥናት ትኩረት ሴቶችንና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረገ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ቢሆንም ወንዶችን ኢላማ ያደረጉ ጥላቻ ንግግሮችም ተተርጉመዉ እዚህ ጥናት ዉስጥ ተካተዋል። ሲ.አይ.አር የጥቃት ሰለባዎቹን ፆታ ማረጋገጥ አይችልም። ለምሳሌ የአዉደ ጥናት ተሳታፊዎች እንደገለፁት ጥቃት ፈፃሚዎች ወንዶች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ሲፈፅሙ የጥቃት ሰለባዎቹን በሴት የመጥራት አዝማሚያዎች አሉ። ዉጤቶቹን ስናይ ይህን ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል።

ይህ መረጃ የተሟላ ባይሆንም በፆታዎች መሃል ያለዉን የጥላቻ ንግግር አይነትና አዉድ ልዩነት ለማየት እንደመነሻ ያገለግላል። በሁለቱ ፆታዎች ላይ በሚደርሱ የጥላቻ ንግግሮች መሃል የመልክ ልዩነት ቢኖርም 'ስድብ' በአብዛኛው የታየው የጥላቻ ንግግር አይነት ነበር። በ'አዉድ' ዙሪያ ያለዉ መረጃ ግን የተለየ ነበር።

### 4.3.1. የጥላቻ ንግግር ከፆታ አንፃር

ከሁለቱ ፆታዎች ሴቶች (77.8 ከመቶ) ከወንዶች (22.2 ከመቶ) በላይ የጥላቻ ንግግር ይደረስባቸዋል። ፆታን መሰረት ካደረጉት የቁልፍ ቃላት ስብስብ መረዳት እንደሚቻለዉ ይህ ጥናት በሴቶች ላይ የሚደርሰዉን የጥላቻ ንግግር


ለመረዳት የተዘጋጀ ነዉ። በመሆኑ የመረጃ ስብስቦቹ ሴቶች ከወንዶች በላይ ጥቃት እንደሚደርስባቸዉ ማንፀባረቃቸዉ የሚገርም አይደለም።




*ምስል 13: የጥላቻ ንግግር ከፆታ አንፃር ያለውን ሰብጥር የሚያሳይ ምስል*

### 4.3.2. የጥላቻ ንግግር አይነቶች በፆታ

ትኩርት በሚስብ ሁኔታ የጥላቻ ንግግር አይነቶች በፆታ ይለያያሉ። ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች 'ስድቦች' ከሌሎች የጥላቻ ንግግር አይነቶች የበለጠ ታይተዋል። ወንዶች ከደረሱባቸዉ የጥላቻ ንግግሮች ዉስጥ ስድቦች ግማሽ አካባቢ የሚሆነዉን ይይዛሉ። ሆኖም ግን ሌሎቹ የጥላቻ ንግግር አይነቶች በሙሉ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ በብዛት ይታያሉ። ለምሳሌ ሴቶችና ልጃገረዶች ከወንዶች የበለጠ አሳናሽ/የበታችነትን የሚሰብኩ የጥላቻ ንግግሮች በብዛት (22.2 ከመቶ ለሴቶች 13.8 ከመቶ ለወንዶች) ይደረሱባቸዋል። ሴቶች (13.5 ከመቶ) ከወንዶች (9.2 ከመቶ) በለይ 'ዛቻ' የያዙ ንግግሮችን ያስተናግዳሉ። ሴቶችና ልጃገረዶች (27.7 ከመቶ) 'ፆታን ከባህሪ ጋር የሚያያይዙ' የጥላቻ ንግግሮች ከወንዶች (26.3 ከመቶ) በትንሹም ቢሆን በበለጠ መልኩ ይደርስባቸዋል።





*ምስል 14: የጥላቻ ንግግር አይነቶች በፆታ ያላቸውን ስብጥር የሚያሳይ ምስል*

### 4.3.3. የጥላቻ ንግግር አዉዶች በፆታ

ሲ.አይ.አር የጥላቻ ንግግር አዉዶች (ጠብ ጫሪ፣ አፀያፊ፣ ፌዝ ወይም በስርዓተ-ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶች) በፆታ ላይ ያላቸዉን ልዩነትም አጥንቷል። ይህም በሁለቱ ፆታዎች መሃል ሰፊ የሆነ የጥላቻ ንግግር አዉዶች ልዩነት እንዳለ ለመረዳት አስችሏል። ለምሳሌ ወንዶች (72.7 ከሞቶ) ከሴቶችና ልጃገረዶች (46.2 ከመቶ) የበለጠ አፀያፊ የጥላቻ ንግግር ይደርስባቸዋል።

ሴቶች በፆታ ሚናቸዉ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁ የጥላቻ ንግግሮች በሰፊዉ (26.2 ከመቶ) ይደርስባቸዋል። ወንዶች ይህን አዉድ ያላቸዉ የጥላቻ ንግግር ከሴቶችና ልጃገረዶች ባነሰ ቢደርስባቸዉም በወንዶች ላይ ከሚደርሱ የጥላቻ ንግግር አዉዶች በ11.7 ከመቶ ሁለተኛዉን ደረጃ ይይዛል።


በመጨረሻም 'ጠብ ጫሪ' የሆኑ ንግግሮች በሁለቱም ፆታዎች ላይ በትንሹ የሚታየዉ የጥላቻ ንግግር አዉድ ነዉ። ወንዶችም (7.8 ከመቶ) ሆነ ሴቶች (7.3 ከመቶ) ተቀራራቢ የሆነ ጠብጫሪ የሆነ የጥላቻ ንግግሮች ይደርሱባቸዋል።




*ምስል 15: የጥላቻ ንግግር አውዶች በፆታ ያላቸውን ስብጥር የሚያሳይ ምስል*

### 4.3.4. የጥላቻ ንግግርና የፆታ ንውስ ቡድኖች ግንኙነት በመድረክ

ከዚህ በፊት እንደተገለፀዉ በሁሉም የተጠኑት የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ሴቶችና ልጃገረዶች ከወንዶች የበለጠ የጥላቻ ንግግር ሰለባ ናቸዉ። ሆኖም ግን በተለያዩ መድረኮች ላይ በሚደርሱት የጥላቻ ንግግሮች መሃል የመጠን ልዩነት አለ። ወንዶች ላይ የሚደርሱት የጥላቻ ንግግሮች በአብዛኛዉ በፌስቡክ ላይ (ፌስቡክ ካሉ ጥቃቶች 40.1 ከመቶ) የሚደርሱ ሲሆን ኤክስ በ17.7 ከመቶ ቴሌግራም ደግሞ በ3.1 ከመቶ ተከታዩን ደረጃ ይይዛሉ።




*ምስል 16: የጥላቻ ንግግርና የፆታ ንውስ ቡድኖች ግንኙነት በቴሌግራም፣ ፌስቡክና ኤክስ ላይ*

### 4.3.6. ማብራሪያ፡ የጥላቻ ንግግር በፆታ ንዑስ ቡድኖች

በፆታዎች መካከል ያለዉን የጥላቻ ንግግር ልዩነት ማጥናት አስፈላጊ ነዉ። ለምሳሌ ወንዶች ከሴቶችና ልጃገረዶች አንፃር ያነሰ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ ንግግሮችና ስላቃዊ ንግግሮች ሲደረሱባቸው የበለጠ ጠብ ጫሪ እና አፀያፊ ንግግሮች ይደርስባቸዋል። ሲ.አይ.አር ከዚህ በፊት ባዘጋጀው ጥናት መሠረት ወንዶችና ሴቶች የተለያዩ የጥቃት አይነቶች ሲደርስባቸው ሴቶች በፆታዊ ሚናቸው ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙ የጥላቻ ንግግሮች ይደርስባቸዋል። የአውድ ጥናቱ ተሳታፊዎች ይህን ሀሳብ በማጠናከር ወንዶች በአብዛኛው ባላቸው የፖለቲካ አመለካከት ጥቃት ሲደርስባቸው ተመሳሳይ ቦታ ላይ ያሉ ሴቶችና ልጃገረዶች ግን በመልካቸውና ማህረሰብ ውስጥ ባላቸው ሚና የጥቃት ሰለባ እነደሚሆኑ ገልፀዋል።

እነዚህ ውጤቶች በአውደ ጥናቱ ላይ ከቀረቡ በኋላ አንድ ተሳታፊ ኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ሴቶች መብት ማውራትና በሴቶች መብት ዙሪያ እንቅስቃሴ ማድረግ እንደ ምዕራባዊ ሃሳብ ከመታየቱም በላይ የኢትዮጵያዊነት እሴትን የሚያወርዱ ተደርገው እንደሚወሰድ ገልፃለች። ስለዚህ ጥቃት አድራሾች በኢንተርኔት ላይ የሴቶች መብት የሚደግፉ ሴቶች ላይ ትችት፣ ጥቃት ወይም ፌዝ ሊሰነዝሩባቸው ይችላሉ። ትኩረትን በሳበ መልኩ 'የኢትዮጵያ እሴቶች ምንን ያካትታሉ?' እና 'የሴታዊት እንቅስቃሴ አነዚህን እሴቶች እንዴት ይጎዳሉ?' በሚሉት ጉደዮች ላይ ውይይት ተነስቶ ነበር። በዚህም የኢትዮጵያ እሴቶችና ፆታዊ ሚናዎች ከቦታ ቦታ ሰፊ ልዩነት እንዳላቸው መስማማት ላይ ተደርሷል። አንድ ተሳታፊ ኢትዮጵያ ውስጥ በስርዓተ ፆታ ሚናዎች ዙሪያ ያለውን ልዩነቶች ማሳየት ማህበረሰቡ ስለሴቶች ያለው አመለካከት ለመቀየር ጠቃሚ እንደሆነ አንስታለች።


ሲ.አይ.አር ፌስቡክ ከሌሎች ማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች በበለጠ ወንዶች ላይ ያነጣጠሩ ጥላቻ ንግግሮች የሚታዩበት መድረክ መሆኑን ተረድቷል። ለዚህም የተረጋገጡም ባይሆኑም ብዙ ምንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ ፌስቡክ፣ ከትዊተር ይልቅ ብዙ ሴት ተጠቃሚዎች ስላሉት በፆታ ዙሪያ ያለው የጥላቻ ልዩነቱ ፅንፍ የወጣ ላይሆን ይችላል።

## 4.4 ከሌሎች የጥላቻ ኢላማዎች ጋር ንፅፅር

በተደራራቢ ጥቃቶች (የጥላቻ ንግግር የተለያዩ ማንነቶችን በአንዴ ሲያጠቃ) ዙሪያ ያለውን ጥያቄ ለመመለስ ሲ.አይ.አር በኢትዮጵያ መንግስት የጥላቻ ንግግር ትርጓሜ መሠረት ሌሎች ማንነቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ተመልክቷል። ትኩረትም በሚስብ መልኩ ከለላ ከተሰጣቸው ማንነቶች ውስጥ ብሔር በጥቃት ኢላማነት የመጀመሪያውን ደረጃ ሲይዝ ፆታ ሁለተኛውን ደረጃ ይዟል። በጥላቻ ንግግር ኢላማዎች ላይ በሚደርሱ ጥቃቶች መካከል ያለውን የአይነትና የአውድ ልዩነት ማወዳደር ሴቶችና ልጃገረዶች የሚደርስባውቸው ጥቃቶችን መልክ ልዩነት ያሳያል። 'ዛቻ' እና 'ጠብጫሪ' የሆኑ የጥላቻ ንግግሮች ከሌሎች የጥላቻ ኢላማዎች አንፃር ሴቶች ላይ ባነሰ ሁኔታ ቢታዩም 'አሳንሰው የሚያዩ' እና 'በፆታዊ ሚና ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካቶችን' የሚያንፀባርቁ ንግግሮች ወይም 'ስላቅ' የያዙ የጥላቻ ንግግሮች ግን በከፍተኛ ሁኔታ ይታያሉ።

### 4.4.1. ህጋዊ ከለላ ያገኙ ማንነቶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች

ይህ ጥናት በአብዛኛው በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሠረት የደረጉ ጥቃቶች ላይ ቢያተኩርምና የተዘጋጀው የቁልፍ ቃላት ስብስብ ከብሔር (9.1 ከመቶ) እና ከሃይማኖት (9.3 ከመቶ) ይልቅ ፆታ ነክ (99.4 ከመቶ) ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ቢሆንም ሲ.አይ.አር ሌሎች ማንነቶችን የሚያጠቁ የጥላቻ ንግግሮችን አግኝቷል። የቁልፍ ቃላቶቹ ስብስብ 'ጠብ ጫሪ' የሆኑ ወይም በጥላቻ ንግግር ውስጥ ጥቅም ላይ ልውሉ የሚችሉ ቃላቶችን የያዘ ነው። ከመረጃ ትርጓሜ በኋላ በትርጓሜ ፕሮተቶኮሉ መሠረት ጥላቻ ንግግር ተብለው የተሰየሙት ብቻ ለትንታኔ ናሙና ውስጥ ተካተዋል። ይህም ሌሎች ማንነቶችን (ብሔር፣ ዘርና የመሳሰሉት) ኢላማ ያደረጉ ጥቃቶችን ያካተተ ነበር። ከአጠቃላዩ የመረጃ ስብስብ 44.5 ከመቶ የሚሆኑት የብሔር ጥላቻን የሚወክሉ ሲሆን 30.2 ከመቶ ፆታን ኢላማ ያደረጉ ጥላቻ ንግግሮች 17.5 ከመቶ ደግሞ ከሃይማት ጋር የተያያዙ ጥላቻ ንግግሮች ናቸው። የዘር ጥላቻና አካል ጉዳተኞችን ኢላማ ያደረጉ ጥቃቶች አነስተኛወን ድርሻ ይወስዳሉ(4.6 ከመቶና 0.3 ከመቶ እንደቅድምተከተላቸው)።





*ምስል 17: የጥላቻ ንግግር ስብጥር ከማንነቶች ጋር የሚያሳይ ምስል*

### 4.4.2. የጥላቻ ንግግር ከጥላቻ ኢላማ ንዑስ ቡድኖች አንፃር

በእያንዳንዱ ከለላ ያለው ማንነት ስር ያሉ ንዑስ-ቡድኖች እንደ ጥቃት ኢላማ ለይተን ስንመለከት የተለዩ ውጤቶችን እናገኛለን። ሴቶችና ልጃገረዶች ከአጠቃላይ የጥቃት ንግግሮች 21 ከመቶውን በመያዝ ከሌሎች ንዑስ ቡድኖች በበለጠ ጥቃት ሲደርስባቸው ኦሮሞዎች 19.2 ከመቶና አማራዎች 16.8 ከመቶ በመያዝ በቅርብ ይከተላሉ። ይህ ጥናት በፆታ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ይህ ተጠባቂ ነው።

ከተገኙት መረጃ ውስጥ በአነስተኛ መጠን ቢሆንም ኦርቶዶክስ ክርስትያኖች (8.8. ከመቶ)፣ ወንዶች(5.9 ከመቶ)፣ ትግሬዎች (5.5 ከመቶ)፣ ሙስሊሞች(4.5 ከመቶ) እና ጥቁሮች (1.3 ከመቶ) የጥቃት ኢላማ ነበሩ።

'ተጨማሪ የጥቃት ኢላማዎች' የሚለው ምደባ በጥቃት ኢላምነታቸው ከ1-10 ደረጃ ካሉት ውጪ የያዘ ሲሆን ፕሮቴስታንቶችን፣ ነጮች፣ ግብረሰዶማውያንን፣ ኢአማንያንን፣ አረቦችን፣ ብዙ ዘር ያላቸውን ሰዎች (Multiracial) እና አይሁዶችን ያካተተ ነው። 'ሌሎች ኢላማዎች' የሚለው ምድብ ደግሞ ከለላ ያላቸውን ቡድኖችን ኢላማ ያደረገ ጥቃት ቢኖርም አንዱ ምድብ ውስጥ ለይቶ ማስቀመጥ ሳይቻል ሲቀር ጥቅም ላይ ውሏል።





*ምስል 18: የጥላቻ ንግግሮች በስምንት ንዑስ ቡድን ኢላማዎች ላይ ያለው ስብጥር*

## 4.4.3. የጥላቻ ንግግር አይነቶች ንፅፅር

ሲ.አይ.አር የጥላቻ ንግግሮችን መጠን ከማጥናት በተጨማሪ በሴቶችና ልጃገረዶች ላይና በሌሎች የማንነት ቡድን ኢላማዎች ላይ በሚደርሱት ጥቃቶች መካከል ያለውን ልዩት ለማየት ሞክሯል። በሰፊው ጥቃት የሚደርስባቸው 6 ንዕስ ቡድኖች በዚህ ንፅፅር ላይ ተካተዋል።

ሴቶች (36.6 ከመቶ) ከአማራዎች (31.4 ከመቶ) ፣ ከሙስሊሞች (29.5 ከመቶ) እና ኦሮሞዎች (22.5 ከመቶ) የበለጠ የስድብ ጥላቻ ንግግር ሲደርስባቸው ከትግሬዎች (45.2 ከመቶ) ያነሰ የስድብ ጥላቻ ንግግር ይደርሱባቸዋል። በተጨማሪም ሴቶች (22.2 ከመቶ) በንፅፅር ከፍ ያለ 'አሳንሰው የሚያዩ' የጥላቻ ንግግሮች ሲደርስባቸው ሙስሊሞች (16.4 ከመቶ)፣ አማራዎች( 13.2 ከመቶ)፣ ትግሬዎች (13 ከመቶ) እና ኦሮሞዎች (9.9 ከመቶ) እንደየቅደምተከተላቸው ተከታዩን ደረጃ ይይዛሉ።

በተቃራኒው ሴቶች (13.5 ከመቶ) በንፅፅር ከኦሮሞዎች (26.1 ከመቶ)፣ ከአማራዎች (24.6 ከመቶ) ከትግሬዎች(22.6 ከመቶ) እና ከሙስሊሞች(18 ከመቶ) ያነሰ የዛቻ ጥላቻ ንግግር ይደርስባቸዋል፡፡




*ምስል 19: የጥላቻ ንግግር በደረጃ ከአንድ እስከ አምስት ባሉ ኢላማዎች ላይ ያለው ስብጥርና የጥላቻዎቹ አይነት*

## 4.4.4. የጥላቻ ንግግር አውዶች ንፅፅር

ሴቶችና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ ጥቃቶች 'አውድ' ሌሎች ቡድኖች ላይ ከሚደርሰው የጥላቻ ንግግር ጋር ሲወዳደር ልዩነቶች አሉ፡፡

ሲ.አይ.አር በሁሉም የጥቃት ኢላማዎች ዘንድ 'አፀያፊ' የጥላቻ ንግግሮች በሰፊው የሚታየው የጥላቻ ንግግር አውድ እንደሆነ ተረድቷል፡፡ ሴቶችና ልጃገረዶች (46.2 ከመቶ) ከፍተኛ መጠን ያላቸው አፀያፊ የጥላቻ ንግግሮች ቢደርስባቸውም ከሌሎች የጥቃት ኢላማዎች ጋር ሲወዳደር ግን ያነሰ ነው፡፡

ከአፀያፊ ንግግሮች በተቃራኒ  በማህበራዊ ሚና ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁ የጥላቻ ንግሮች በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ በአብዛኛው ይታያሉ (26.2 ከመቶ)፡፡ እነዚህ የጥላቻ ንግግሮች በሙስሊሞች (12.5 ከመቶ)፣ አማራዎች (9.3. ከመቶ)፣ ኦሮሞዎች(5 ከመቶ) እና ትግሬዎች(2.7 ከመቶ) ላይ ከሴቶች በመቀጠል ይንፀባረቃሉ፡፡

ከሴቶች (20.4 ከመቶ) በላይ የስላቅ የጥላቻ ንግግር የሚደርስባቸው ሙስሊሞች (21.3 ከመቶ) ብቻ ናቸው። ሴቶች ከትግሬዎች (11.5 ከመቶ)፣ አማራዎች (6.9 ከመቶ) እና ኦሮሞዎች (5 ከመቶ) የበለጠ የስላቅ አውድ ያለው የጥላቻ ንግግር ይደርስባቸዋል።

በመጨረሻም ሲ.አይ.አር ሴቶች ከሌሎች ኢላማዎች በንፅፅር ዝቅተኛ 'ጠብጫሪ' አውድ ያላቸው የጥላቻ ንግግሮች እንደሚደርስባቸው በጥናቱ አይቷል።





*Figure 20: የጥላቻ ንግግር በደረጃ ከአንድ እስከ አምስት ባሉ ኢላማዎች ላይ ያለው ስብጥርና የጥላቻዎቹ አውድ*

### 4.4.5. ማብራሪያ፡ ከሌሎች የጥላቻ ኢላማዎች ጋር ንፅፅር

ይህ ጥናት ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግር ሌሎች ማንነቶችን ኢላማ ካደረጉ ጥቃቶች በአይነትና በአውድ ልዩነት እንዳላቸው አሳይቷል። ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥላቻ ንግግሮች ስውር በሆነ መልኩ የሚፈፀሙና ለዘብ ያሉ ናቸው። ለምሳሌ ሴቶችና ልጃገረዶች ከሌሎች የጥቃት ኢላማ ቡድኖች አንፃር 'አሳንሰው የሚያዩ' እና 'በስርዓተ ፆታ ሚና ዙሪያ የተሳሳቱ አስተሳሰቦችን' የሚያንፀባርቁ ወይም 'ስላቅ' የበዛባቸው፤ 'ጠብጫሪ' እና 'አፀያፊ' ይዘታቸው አነስ ያሉ የጥላቻ ንግግሮችን ያስተናግዳሉ። እነዚህ ግኝቶች ሲ.አይ.አር ከዚህ በፊት ባካሔደው ጥናት ላይ ከተነሱት ሀሳቦች ጋር ይደጋገፋሉ። በቀደመው ጥናት ላይ ሴቶች ባላቸው ሚና ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁና

ከመልካቸው ጋር የተያያዙ ጥቃቶች እንደሚደርስባቸው ተነስቶ ነበር ለምሳሌ ሴቶች በፀጉራቸው ፣ በአለባበሳቸው፣ በሰውነታቸው ክብደት ፣ በትዳር ሁኔታቸው በሚጠረጠሩበት የፍቅር ግንኙነነት እና በልጆቻቸው ብዛት የማህበራዊ ሚዲያ መከራከሪያ እንደሆኑና ይህ ተመሳሳይ በታ ላይ ወንዶች ላይ እንደማይታይ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ገልፀው ነበር። ይህ እንደ 'ዛቻዎች' እና 'ጠብ ጫሪ' ንግግሮች ያህል ጎጂ ባይመስልም የተሳሰቱ ትርክቶችን በማስቀጠልና ሴቶችና ልጃገረዶች የእኩል እድል ተጠቃሚ አንዳይሆኑ በማድረግ ለፆታ እኩልነት እንቅፋት ይሆናሉ። የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች እነዚህ ጥቃቶች የተንሰራፉና የተለመዱ መሆናቸውን ገልፀዋል ።

ፆታን መሰረት ያደረገ የጥላቻ ንግግር በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ብቸኛው የጥላቻ ንግግር አይነት እንዳልሆነ ግልፅ ነው። የሲ.አይ.አር መርማሪዎች የሀይማኖትና የብሔር ጥላቻ ንግግሮች በመስፋፋታቸው ምክንያት በሀገሪቷ ውስጥ በስብዓዊ መብት ሴክተር ላይ ለሚሰሩ ሁሉ ፈተና እንደሆነ ይረዳሉ። እያንዳንዱ ቡድን በሚደርስበት የጥላቻ ንግግር አይነቶች መሀክል ያለውን ልዩነት መረዳት የተሻሉ የፖሊሲ መፍትሔዎችን ለመስጠት መነሻ ነው ።

አሁናዊ ሁነቶች ይህ ጥናት ላይ ተፅዕኖ ፈጥረዋል። መረጃዎች በሚተረጎሙበት ወቅት አማራ ክልል ውስጥ የነበረው ግጭት ኢንተርኔት ላይ ላሉት ጠብ ቀስቃሽ ንግግሮች መነሻ እንደሆነ ታይቷል። በተመሳሳይ ሲ.አይ.አር ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ በኦሮሞነታቸው ምክንያት የጥላቻ ንግግር እንደሚደርስባቸው ተመልክቷል። እንደዚህ አይነት በፖለቲካ ሁነቶች ምክንያት የሚፈፀሙ የጥላቻ ንግግሮች በልዩ ተፈጥሯቸው ምክንያት ፆታን መሰረት ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች የበለጠ ትኩረት ሊስቡ ይችላሉ። በፆታ ዙሪያ የተሳሰቱ ሚናዎችን የሚያንፀባርቁና አሳንሰው የሚያዩ ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ትኩረት አይሰጣቸውም። እንደ አውደ ጥናቶቹ ተሳታፊዎች ችግሩ እጅጉን ከመስፋፋቱ የተነሳ በጣም የተለመደና የማይታይ እየሆነ መጥቷል ።


ሁሉም አይነት የጥላቻ ንግግሮች በግልም ሆነ በቡድን ደረጃ የጥቃቱ ሰለባዎች ላይ ዘላቂ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ። ይህ ጥናት ፆታ ላይ ያተኮረና መፍትሔ ሀሳቦቹም በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ለመከላከል የቀረቡ ቢሆንም አንዳንድ መፍትሔ ሀሳቦች ግን ሌሎች ኢላማዎች ላይ የሚደርሱ የጥላቻ ንግግሮችን ለመከላከል ያግዛሉ።

## 4.5 ተደራራቢ ፆታን መሰረት ያደረገ የጥላቻ ንግግር

በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚደርሱ የተደራረቡ የጥላቻ ንግግሮች አውድን ለመረዳት ሲ አይ አር ሴቶችንና ልጃገረዶችን ከሌሎች ማንነቶቻቸው ጋር ደርበው የሚያጠቁ የጥላቻ ንግግሮችን አጥንቷል። በጥምር ስለሚጠቁት ማንነቶችና ስለ ጥቃቶቹ አይነትና አውድ ከዚህ በታች በዝርዝር ተቀምጧል ። እንደሚጠበቀው ከፆታ ጋር ተያይዞ የተጠቃው ማንነት ሲለያይ የጥቃቶቹ አውድና አይነትም ይለያያሉ ።

### 4.5.1. ተደራራቢ የጥላቻ ንግግሮች

በአጠቃላይ መረጃ ሰብስብ ውስጥ ሴቶችና ልጃገረዶች ከሌሎች 6 ማንነቶቻቸው ጋር በጥምር ጥቃት ደርሶባቸዋል። ማንነቶቹም ብሔሮች (ኦሮሞ እና አማራ) ፣ ዘር (ጥቁር) እና ሀይማኖት (ኦርቶዶክስ) ናቸው ።




*ምስል 21: ሴቶች ከሌላ ማንነታቸው ጋር ሲጠቁ ያለውን የተደራራቢ ጥላቻ ንግግር ስብጥር የሚያሳይ ምስል.*

### 4.5.2. የተደራራቢ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃት አይነቶች

የጥቃቶቹም አይነት ከፋፍለን ስንመለከት በጥቃቶቹ አወቃቀር መሀል ያለውን ግልፅ ልዩነት መመልከት እንችላለን 'ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ብቻ' (ክፍል 4.1) ከሚደርሱት የጥላቻ ንግግሮች በተለየ መልኩ 'ስድቦች' በጥላቻ ንግግር አይነት የመጀመሪያውን ደረጃ አይይዙም።

ፆታ ከሁለቱ የጥላቻ ንግግር ብሔር ኢላማዎች (አማራ እና ኦሮሞ) ጋር ሲጠቃ 'አሳንሰው የሚያዩ' የጥላቻ ንግግር አይነቶች ሰፊውን ድርሻ ይወስዳሉ። ይህም ማለት በፆታቸው እና በብሔራቸው ምክንያት በማህበራዊ ተዓማኒነታቸው፣ በአስተሳሰባቸው ወይም በአካላዊ ብቃታቸውና ተፈላጊነታቸው እኩል እንዳልሆኑ ወይም ዝቅ ተደርገው ታይተዋል ።

በኦርቶዶክስና ፆታ ላይ መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ደግሞ በአብዛኛው ማነነትን ከአንድ ባህሪ ጋር የሚያያዙ ናቸው። ይህም ማለት በፆታቸውና በሀይማኖታቸው ብቻ በመመርኮዝ ስለሴቶችና ልጃገረዶች የግል ባህሪ ግምቶች ተቀምጠዋል ማለት ነው ።

በዚህ ጥናት ላይ ከተለያዩ ሌሎች የጥላቻ ንግግሮች በተቃራኒ 'ዛቻዎች' በዛ ያሉ ተደራራቢ የሆኑ የጥላቻ ንግግሮች ላይ ታይቷል። ለምሳሌ 'ዛቻዎች' 'ሴቶችና ኦርቶዶክስ' ቡድን ላይ ከሚደርሰው የጥላቻ ንግግር አይነት 25 ከመቶውን ሲይዝ 'ሴቶችና ጥቁሮች' ላይ ከሚደርሰው ጥቃት ላይ ደግሞ 22.5 ከመቶውን ይይዛል። በክፍል 4.1 ላይ እንደታየው ሴቶችን ብቻ ኢላማ ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች አይነቶች ውስጥ ዛቻዎች 13.5 ከመቶውን ብቻ ነበር የያዙት፤ ስለዚህም ጥቁር ወይም ኦርቶዶክስ ተብለው የተወከሉ ሴቶች የዛቻ አይነት ያላቸው የጥላቻ ንግግሮች ከሌሎች ቡድኖች በበለጠ ይደርስባቸዋል። ሆኖም ግን እነዚህን ውጤቶች በምንመለከትበት ወቅት በጥናቱ ዘዴ ዙሪያ ያሉ ቅድመ ሁኔታዎችን መገንዘብ ይኖርብናል።





*Figure 22: ምስል 23: ሴቶች ከሌላ ማንነታቸው ጋር ሲጠቁ ያለውን የጥላቻ ንግግር አይነት ስብጥር የሚያሳይ ምስል*

.


### 4.5.3. የተደራራቢ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃት አውዶች

በተመሳሳይ የተደራራቢ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች አውድን በምንመለከትበት ጊዜ የተለያዩ ውጤቶችን እናገኛለን። ሴቶችና ልጃገረዶችን ብቻ ኢላማ ካደረጉ ( ክፍል 4.1.2 ) የጥላቻ ንግግሮች አውድ በተመሳሳይ መልኩ እነዚህም 'አፀያፊ' ንግግር ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል ።

'አፀያፊ' የጥላቻ ንግግር 'ሴቶችና ኦሮሞ' ንዑስ ቡድን ላይ የሚሰነዘረው ብቸኛው ጥላቻ ንግግር አውድ ሲሆን ይኸው አውድ 'ሴቶችና ልጃገረዶች እና አማራ' ንዑስ ክፍል ላይ ከሚሰነዘረው የጥቃት አውድ ውስጥ 57 ከመቶውን ብቻ ይይዛል። ይህ ልዩነት በኦሮሚያ እና አማራ ክልል ውስጥ ባሉ ግጭቶች ምክንያት የመጣ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል ።

ሌሎች ትኩረት የሚስቡ ውጤቶችም ነበሩ። ለምሳሌ በስነፆታዊ ሚና ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁ የጥላቻ ንግግሮች በተለያዩ የጥላቻ ኢላማ ንዑስ ቡድኖች ላይ የተለያዩ በበሩ። 'ሴቶችና ልጃገረዶች

እና ኦሮሞ' ንዑስ ቡድን ላይ ይህ የጥቃት አውድ ያልታየ ሲሆን 'ሴቶችና ልጃገረዶችና እና ጥቁር' ንዑስ ቡድን ላይ ከሚደርሱባቸው የጥላቻ ንግግር አውዶች አንድ ሶስተኛውን ይይዛል። ከ 'ሴቶችና ልጃገረዶች እና ኦርቶዶክስ' ንዑስ ቡድን ውጪ ያሉት ሁሉም ንዑስ ቡድኞች 'ሴቶችና ልጃገረዶች ብቻ' ላይ ከሚደርሰው 'የስላቅ' አውድ የጥላቻ ንግግር ያነሰ ይደርስባቸዋል። በመጨረሻም 'ሴቶችና ልጃገረዶች እና አማራ' ንዑስ ቡድን 'ሴቶችና ልጃገረዶች ብቻ' ላይ  ከሚደርሰው ጥቃት ጋር ሲወዳደር የበለጠ 'ጠብ ጫሪ' አውድ ያላቸው የጥላቻ ንግግሮች (14.3 ከመቶ) ይደርሱባቸዋል።




*ምስል 23: ሴቶች ከሌላ ማንነታቸው ጋር ሲጠቁ ያለውን የጥላቻ ንግግር አውድ ስብጥር የሚያሳይ ምስል*

### 4.5.4. ማብራሪያ

ትኩረት በሳበ መልኩ 'ሴቶችና ልጃገረዶችን ብቻ' ኢላማ ባደረጉ ጥቃቶችና ሴቶችን ከሌላ ማንነታቸው ጋር ደምረው ኢላማ በሚያደረጉ ጥቃቶች መካከል ልዩነቶች አሉ። የፖለቲካ ሁነቶች፣ ኢንተርኔት ላይ የሚነሱ የውይይት ርዕሶችና የሀሳብ ልውውጦች ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ ። ከላይ እንደተገለፀው አማራ ክልል ውስጥ የነበረው ግጭት ይህ ጥናት በተሰራበት ወቅት በኢንተርኔት ላይ ዋነኛ የመነጋገሪያ ርዕስ ነበር። አማራ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ያነጣጠሩት

ጥቃቶች በዚህ ግጭት ላይ የተመረኮዙ ሊሆን ይችላሉ፤ ይህ አስተያየት በተመሳሳይ የኦሮሞ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይም ይሰራል። ይህ ሆኖ ሳለ በኦሮሞና አማራ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ በደረሱት ጥቃቶች መካከል ያለው ግልፅ የሆነ የአውድ ልዩነት በፖለቲካና ግጭት ብቻ ሊብራራ አይችልም። አማራ ሴቶች ከኦሮሚያ ሴቶች በበለጠ መልኩ ጠብጫሪ ወይም በሚናቸው ዙሪያ ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች የያዙ እና ስላቅን የያዙ ንግግሮች ይደርስባቸዋል ። ይህም የመረጃ የጉዳዩን ውስብስብነት ያሳያል። ወደፊት የሚሰሩ ጥናቶች ከእነዚህ ልዩነቶች ጀርባ ያሉትን ምክንያቶች ሊያጠኑ ይችላሉ በተመሳሳይ በትግራይ ጦርነት ወቅት የትግራይ ሴቶች ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶች ጨምረው እንደነበር ለማወቅ ጥናቶችን መስራት ይቻላል ።

በተመሳሳይ፣ ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ጥላቻ ንግግሮች በሰፊዉ ይታያሉ። በጥናቱ ወቅት በኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ዉስጥ መከፋፈል ተፈጥሮ ስለነበር አብዛኛዎቹ የኢንተርኔት ላይ ዉይይቶች ሃይማኖታዊ ይዘት ነበራቸዉ። ይህም አሁናዊ ከኢንተርኔት ዉጪ ያሉ ሁነቶች ኢንተርኔት ላይ በሚፈፀሙ ጥቃቶች ላይ ቀጥታኛ ተፅዕኖ እንዳላቸዉ የሚያትተዉን ሃሳብ ያጠናክራል። በዚህም ምክንያት ከኢንተርኔት ዉጪ ፖለቲካዊ፣ ብሔር ተኮርና ሃይማኖታዊ ዉጥረቶች ሲኖሩ ፖሊሲ አዉጪዎች አንድን ቡድን ኢላማ ያደረጉ የኢንተርኔት ላይ ጥቃቶች እንዳይጨምሩ ለመከላከል መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ስለሆነም የቅድመ መከላከልና የድህረ መከላከል ዘዴዎች የጥላቻ ንግግርን ለመከላከል አስፈላጊ ናቸዉ። አንድ የአዉድ ጥናት ተሳታፊ እንዳስተዋለችዉ አለመረጋጋትና ግጭቶች በሚኖሩበት ወቅት የጥላቻ ንግግሮችን ለመቀነስ ከመስራት ይልቅ አሁን ያለዉ ፖሊሲ ኢንተርኔትን መዝጋት ነዉ። ይህ መደረጉ ዉጥረት በማስፈን የሚተቹትን የዲያስፖራዎች ድምፅ በማጉላት ለሰላም ጠር ይሆናል የሚል እምነታቸዉን ተሳታፊዎች አክለዋል። በሁሉም አዉደ ጥናት ላይ በሚባል ሁኔታ ተሳታፊዎች የዲያስፖራዉን ሚና ለማሰስ ሲ.አይ.አር የልጥፎቹን መነሻ በታ ማየት እንደሚችል ጠይቀዉ ነበር። ይህ በተመረጠዉ የጥናት ዘዴ ምክንያት ባይቻልም የወደፊት ጥናቶች ይህን ከግምት በማስገባት ሊሰሩ ይችላሉ።


## 4.6 የግብረ ሰዶማዊነት ውንጀላዎች

በስብሰባዎች፣ አውደ ጥናቶች እና የሲ.አይ.አር የመጀመሪያ ጥናት ላይ የተሳተፉ ግለሰቦች ስለሴቶች መብትና በመናገራቸው ምክንያት የግብረ ሰዶማዊነት ውንጀላ እንደደረሰባቸው ተናግረዋል። ለምሳሌ በቀዳሚው ጥናት ላይ ከተሳተፉት የቃለ መጠይቅ ተሳታፊዎች ውስጥ 29 ከመቶ የሚደርሱት በጥቃት ፈፃሚዎች ግብረሰዶም የሚል ስም እንደተሰጣቸው ገልፀዋል። በተለያዩ የኢንተርኔት ፎረሞች ላይ ለሴቶችና ልጃገረዶች መብት የሚሟገቱ የቃለመጠይቅ ተሳታፊዎች የግብረሰዶማዊነት ውንጀላ እንደደረሰባቸው ገልፀዋል። እንደተሳታፊዎቹ እምነት ጥቃት አድራሾቹ የግብረሰዶማዊነት ውንጀላውን አንደስድብ ብቻ የሚጠቀሙት ሳይሆን ደህንነታቸው፣ ነፃነታቸውና በአደባባይ የመናገር ብቃታቸው ላይ የደህንነት ስጋት ለመፍጠር አስበው ያደረጉት ነው። ግብረ ሰዶማዊነት ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነት የሌለው ርዕስ ከመሆኑም በላይ ህገወጥ የሆነና የአንድ አመት እስር የሚያስከትል ተግባር ነው። በዚህም ምክንያት አነዚህ ውንጀላዎች በኢላማዎቹ ላይ ስጋት ይዘው ይመጣሉ።

በዚህ ጥናት ወቅት፣ ሲ.አይ.አር የግብረሰዶም ውንጀላዎችን ጨምሮ ሌሎች ሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ ያነጣጠሩ የጥላቻ ንግግሮችን ለይቷል። በተገኘው መረጃ መሰረት የግብረሰዶም ውንጀላዎችን የያዙ የጥላቻ ንግግሮች ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ብቻ ዒላማ ካደረጉ የጥላቻ ንግግር ይለያሉ። ለምሳሌ የግብረ ሰዶማዊነት ውንጀላዎችን ያካተቱ ሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ ያነጣጠሩ የጥላቻ ንግግሮች ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ብቻ ኢላማ ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች (13.5%) የበለጠ 'ዛቻዎችን' (50%) ይይዛሉ። በተጨማሪም የግብረ ሰዶማዊነት ውንጀላዎችን ያካተቱና

ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ብቻ ኢላማ ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች (7.3%) የበለጠ 'ጠብጫሪ' (40%) ናቸው።

ይህ ግኝት በሲ.አይ.አር ቀዳሚ ጥናትና አዲስ አበባ ውስጥ በተካሄዱት ቀጣይ ስሰባዎችና አውደጥናቶች ላይ በተሳተፉ ግለሰቦች የተነሳውን ሃሳብ የበለጠ በመረጃ ያጠናክራል። በግብረ ሶዶማዊነት የተወነጀሉ ሴቶችና ልጃገረዶች በሴተነታቸው ብቻ ጥቃት ከሚደረስባቸው ሴቶች የበለጠ 'የዛቻ' እና 'ጠብ ጫሪ' የሆኑ የጥላቻ ንግግር ይደርስባቸ




*ምስል 24: የጥላቻ ንግግር ሴቶች ላይ ሲደርስና ሴቶች ላይ ከግብረሰዶማዊነት ውንጀላዎች ጋር ሲደርስ ያለውን ልዩነት የሚየሳይ ምስል*

## 5. መደምደሚያ

የሰዎች ግላዊና ማህበራዊ ህይወት በማህበራዊ ሚዲያ በኩል ኢንተርኔት ላይ በሰፊዉ እየተንፀባረቀ መምጣቱ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል በሚደረገዉ ጥረት ላይ አዲስ ፈተና ይዞ ብቅ ብሏል። የዚህ ጥናት አላማ በሶስት ማህበራዊ መድረኮች ላይ (ኤክስ፣ቴሌግራምና ፌስቡክ) በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚደርሱ የጥላቻ ንግግሮች አይነትን (ስድብ፣ ዛቻ፣ ማንነትን ከባህሪ ጋር ማገኛኘት፣ አሳንሰዉ የሚያዩ)፣ አዉድን (አፀያፊ፣ በስርዓረ ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁ፣ ስላቅ፣ ጠብ ጫሪ) በመመርመር ኢትዮጵያ ዉስጥ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ባደረጉ ጥቃቶች ዙሪያ ያለዉን ማስረጃ ማጠናከር ነዉ። ሲ.አይ.አር ወንዶች ላይ በሚደርሰዉ የጥላቻ ንግግር ዙሪያ ያሉ መረጃዎችን በመሰብሰብ በሁለቱ ቡድኖች ላይ የሚደርሰዉን የጥላቻ ንግግር ለማወዳደር ችሏል። በተደራራቢ ፆታን መሰረት ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች (የጥላቻ ንግግር ከፆታ በተጨማሪ ሌላ ማንነት ሲያጠቃ) ዙሪያ ያሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ሲ.አይ.አር በብሔር፣ በሃይማኖትና በዘር ዙሪያ ያሉ ጥላቻ ንግግሮችንም መርምሯል።

ይህም ሆነ የሲ.አይ.አር የመጀመሪያዉ ጥናት ("በኢትዮጵያ ማህበራዊ ህይወት ላይ ተሳትፎ የሚያረጉ ሴቶች ላይ የሚደርሱ በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች") ሴቶችና ልጃገረዶች ከወንዶች የተለዩ የኢንተርኔት ላይ ጥቃት አይነቶች እንደሚደርስባቸዉ አሳይተዋል። የመጀመሪያዉ ጥናት ላይ በተደረጉት ቃለመጠይቆች መሰረት ሴቶችና ልጃገረዶች በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙና አሳናሽ የሆኑ ጥቃት ሲደርስባቸዉ ወንዶች ላይ የሚደርሰዉ ጥቃት ግን ባላቸዉ አመለካከትና ፖለቲካ ላይ ያተኮረ ነዉ። በተመሳሳይ፣ በዚህ ጥናት ላይ ያለዉ የማህበራዊ ሚዲያ ትንተና እንደሚያሳየዉ ሰቶች ከወንዶች የበለጠ በፆታዊ ሚና ዙሪያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን የያዙና አሽሙር ወይም ስላቅ የያዙ የጥላቻ ንግግር ሲደርስባቸዉ ከወንዶች ያነሰ 'ጠብ ጫሪ' ንግግር እንደሚደርስባቸው ነው።

በነበሩት ዉይይቶችና አዉደ ጥናቶች ላይ በጥላቻ ንግግር ዙሪያ ያለዉ ግንዛቤ የተሳሳተ እንደሆነና ይህም የተወሰኑ አይነት በቴክኖጂ የታገዘ ፆታን መሰረትያደረጉ ጥቃቶች ችላ እንዲባሉ እንዳደረገ ተነስቷል። በተጨማሪም አንዳንድ የጥላቻ ንግግር ይዘቶች ለምሳሌ የተዛባ የስርዕተ ፆታ አመለካከቶች፣ ስድብ፣ አዋራጅ ንግግሮች ወይም የሴቶችና ልጃገረዶችን የበታችነት የሚሰብኩ ንግግሮች፤ ዛቻና ጠብጫሪ ከሆኑ ንግግሮች ያነሰ ጉዳት ያመጣሉተ ብሎ ይታሰባል ወይም እንደ ጥላቻ ንግግር ላይታዩም ይችላሉ። ስለዚህም ስለ ጥላቻ ንግግር ምንነትና ተፅዕኖዎቹ የተሻለ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ነዉ።

የሲ.አይ.አር የመጀመሪያዉ ጥናት ላይ የተሳተፉ አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን ያደረገ ጥቃት በሚጠቀሟቸዉ ሁሉም ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፅ ላይ እንደተመለከቱ ገልፀዋል። ይህ ጥናት በሶስቱ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆች ላይ ሴቶችና ልጃገረዶችን ኢላማ አድርገዉ በሚደርሱ የጥላቻ ንግግሮች መካከል የአዉድ መመሳሰል አንዳለ ቢረዳም የአይነት ልዩነት ግን መኖሩን ተመልክቷል። ለምሳሌ ስድቦች በአብዛኛዉ ፌስቡክ ላይ ሲታዩ ቴሌግራም ላይ በአብላጫዉ ዛቻዎች ይታያሉ። ፌስቡክ ላይ ፆታን ከአንዳንድ ባህሪ (ለምሳሌ ስግብግብነት) ጋር የሚገናኙ ወይም ሴቶችና ልጃገረዶችን ባላቸዉ ማህበራዊ ቦታ ወይም በአስተሳሰባቸዉ ወይም አካላዊ ብቃታቸዉ አሳንሰዉ የሚያዩ የጥላቻ ንግግሮች በሰፊዉ ይታያሉ። ልዩነቶች ቢኖሩም የጥናቱ ዉጤቶች በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጣ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በሶስቱ መድረኮች ላይ እንዳለ አሳይተዋል። እነዚህ ጥቃቶች ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ብቻ የሚደርሱ ሳይሆን ወንዶች ላይም የሚታዩ ናቸዉ።

የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎቹ የተለያዩ ማህበራዊ ትስስር ድህረ-ገፆችን ለተለያዩ ጉዳዮች እንደሚጠቀሙ ተናግረዋል። በመድረኮቹ ዙሪያ ያለዉን ልዩነት (በጥቅማቸዉም ሆነ በሚይዙት የጥላቻ ንግግር) መረዳት ችግሮቹ ላይ ያተኮሩ መፍትሄዎችን ለመስጠትና ሴቶች ራሳቸዉን በተሻለ መንገድ እንዲከለከሉ ያግዛል፤ አንድ የመፍትሄ ሃሳብ ለሁሉም መድረክና ተጠቃሚ ላይሰራ ይችላል። የወደፊት ጥናቶች በሌሎች መድረኮች ላይ ማለትም ዩቲዩብ እና ቲክቶክ ላይ ስላሉ የጥላቻ ንግግር አይነቶችና አዉዶችን ማጥናት ይችላሉ።

በተደራራቢ ጥቃቶች ዙሪያ በተደረገው ጥናት መሰረት ኢንተርኔት ላይ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ የሚደርሰው ጥቃት ሌሎች ማንነቶችን አላማ ከሚያደርጉ ጥቃቶች ጋር ሲደመር ሊጨምር ይችላል። ለምሳሌ ፆታንና ብሔርን መሰረት ያደረገ የጥላቻ ንግግር የሚደርስባቸዉ ሴቶችና ልጃገረዶች በሴትነታቸዉ ብቻ ጥቃት ከሚደርስባቸዉ ሴቶች የበለጠ ዛቻን የያዙና ጠብጫሪ የሆኑ የጥላቻ ንግግሮች ይደርስባቸዋል። ከኢንተርኔት አለም ዉጪ ያሉ አሁናዊ ሁነቶች ኢንተርኔት ላይ ባለዉ ክርክርና ጥላቻ ንግግር ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ የሚለዉ ሀሳብ በዚህ ጥናት ተደግፏል። ለምሳሌ በዚህ ጥናት ወቅት በኦሮሚያና አማራ ክልሎች የነበሩት ግጭቶች ከሌሎች ብሔሮች በበለጠ መልኩ ኦሮሞና አማራ ሴቶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች እንዲበዙ አድርጓል።

የጥናቱ ግኝቶች ሴቶችን ብቻ ሣይሆን ሌሎች የማንነት ቡድኖች ኢላማ ያደረጉ ንግግሮችን ይዘት በልዩ ሁኔታ ያሳያል። ሴቶችና ልጃገረዶች ከብሔርና ሃይማኖት ጥላቻ ኢላማዎች አንፃር አሳንሰዉ የሚያዩ፣ የተዛቡ ስነ ፆታዊ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁ ወይም ስላቅና አሽሙር የያዙ የጥላቻ ንግግር ሲደርስባቸዉ ከሌሎቹ ቡድኖች አንፃር ያነሰ ጠብ ጫሪ ንግግሮች ይደርስባቸዋል። ይህ ጥናት ፆታን መሰረት ያደረገ ጥላቻ ንግግር ላይ ቢያተኩርም በተሰበሰበዉ መረጃ መሰርት ብሔር በጥላቻ ንግግር ኢላማነት ቁጥር አንድ ደረጃ ሲይዝ ፆታ ተከታዩን ደረጃ ይዟል።

በተደራራቢ ጥቃቶች (ፆታ ከአንድ ሌላ ማንነት ጋር አብሮ ማጥቃት) ዙሪያ መረጃ በመሰብሰብ ሴቶችና ልጃገረዶችን ኢላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች፣እንደ ሃይማኖትና ብሔር ካሉ ማንነቶች ጋር በአንድነት ሲፈፀም ያለዉን የጥቃት አዉድና አይነት ልዩነት ማየት ተችሏል። ፖለቲካዊ ሁነቶች ላይ የተመረኮዙና ጠብ ቀስቃሽ የሆኑ ትርክቶችን የያዙ ብሔር ተኮርና ሃይማኖት ተኮር የጥላቻ ንግግሮች፣ ፆታን መሰረት ካደረጉ የጥላቻ ንግግሮች በላይ ትኩረት ይስባሉ። በፆታ ዙሪያ የተሳሳቱ አስተሳሰቦችን የያዙና ሴቶችን አሳንሰዉ የሚያዩ ፆታን መሰርት ያደረጉ ጥላቻ ንግግሮች ትኩረት አይሰጣቸዉም ። እንደ አዉድ ጥናት ተሳታፊዎች እነዚህ ንግግሮች ከመደጋገማቸዉ የተነሳ የተለመዱ ሆነዋል።

ይህ ጥናት የሴቶችና ልጅገረዶችን ተሳትፎን የሚቀንሱ እና የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ላይ የሚለቀቁ ፆታን ያማከሉ የጥላቻ ንግግር ይዘቶችን አጉልቶ ማሳየት ይፈልጋል። ቀደም ያለ በሲ.አይ.አር አር የተደረገ ጥናትም እንደሚያመለክተዉ በኢንተርኔት ጥቃት ደርሶባቸዉ ቃለመጠይቅ የተደረገላቸዉ ሴቶች ጥቃቱ ድምፃቸዉን ከመቀማትም አልፎ በኢንተርኔትም ሆነ በአካል ያላቸዉን ማህበራዊ ተሳትፎ እንዳያከናዉኑ እንዳደረጋቸዉ ዘግበዋል። ደህንነቱ የተጠበቀ የማህበራዊ ሚዲያ መድረክ ሴቶችና ልጃገረዶች ሙሉ አቅማቸዉን በመጠቀም ትርጉም ያለዉ የኢንተርኔት ላይና አካላዊ ተሳትፎ እንዲኖራቸዉ ከፍተኛ አስተወፅኦ አለዉ። በቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚቃጡ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል የሚቀረፁ ስትራቴጂዎች ዘላቂ ዉጤት እንዲያመጡ የችግሮቹን ስር ምክንያቶች መቅረፍ አለባቸዉ። ይህም በፆታ ላይ የተመሰረቱ የተሳሳቱ አመለካከቶች እና መድሎዎችን መቃወም እና የሴቶችና ልጃገረዶችን ውክልና በሁሉም ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ማበረታታትን ያካትታል።

## 6. ምክረ ሀሳቦች

ሲ.አይ.አር በኢትዮጵያ ዉስጥ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ከዚህ ጥናት ጋር አብሮ የሚሄድ ፖሊሲና ማህበረሰብ-መር ምክረ ሃሳቦችን የያዘ ወረቀት አዘጋጅቷል። ይህ ጥናት እንደሚያሳየዉ የጥላቻ ንግግር እንደ ኢላማዉ ይለያያል። እነዚህን ልዩነቶችን መረዳት የሴቶችንና ልጃገረዶች የኢንተርኔት ደህንነት በተሻለ ሁኔታ ለመጠበቅ ለታለሙ የፖሊስ መፍትሄዎች መግቢያ ነጥብ ይሰጣል።

ሲ.አይ.አር የዚህን ጥናት ግኝት የመንግስት ተቋማት ዉሳኔ ሰጪዎችን ለማሳወቅ፣ የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች የኢንተርኔት ይዘት ቁጥጥራቸውን ለማሻሻል፣ የሲቪል ማህበረሰቦች ሙግታቸዉ ዉስጥ በማካተት እና ህብረተሰቡ እርምጃ ለመዉሰድ ይጠቀሙበታል ብሎ ተስፋ ያደርጋል።

Centre for Information Resilience